በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

ከ/ል/ቤ/ሚ/ር 15:2009
የመጀመሪያ ዕትም
06/7/2009

# የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ

መጋቢት 2009 ዓ/ም
አዲስ አበባ

# የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ

## የመጀመሪያ ዕትም

## መጋቢት 2009 ዓ/ም

# ማውጫ


መግቢያ ..... v
1. ወሰን ..... 1
2. ትርጓሜ ..... 1
**ክፍል አንድ፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ..... 4**
3. የፊትለፊት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ..... 4
4. ዝርዝር አገልግሎቶች፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ-ሁኔታዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ..... 6
4.1. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የመደበኛ ቀብር አገልግሎት ..... 6
4.2. የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ መቃብር የራስጌ ምልክት የመትከል አገልግሎት ..... 7
4.3. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የባይተዋር ቀብር አገልግሎት ስታንዳርድ ..... 8
4.4. የስብስብ ቀብር አገልግሎት ስታንዳርድ ..... 9
4.5. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያው ምድረግቢ ውስጥ ስርዓተ ቀብር ስለመፈጸሙ ማስረጃ የመስጠት አገልግሎት ..... 10
4.6. ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት ..... 11
4.7. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ለቁሳቁስ አቅርቦት፣ ለማህበራትና ለግል ድርጅቶች ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት ..... 12
4.8. በዝወውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የመጣ አስከሬን የመቅበር ወይም አጽም የማሳረፍ አገልግሎት ..... 13
4.9. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ ማውጣትና መልሶ መቅበር /exhumation and reburial/ ..... 15
5. መልሶ መቅበር /Reburial by Council/ ..... 16
**ክፍል ሁለት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የማልማት ስታንዳርድ ..... 17**
6. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ልማት ስታንዳርድ ..... 17
6.1. የቦታ መረጣ /site selection/ ስታንዳርድ ..... 17
6.2. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የምድረ ግቢ መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች/ ስታንዳርድ ..... 18
6.3. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ አጥርና የመግቢያ በር ስታንዳርድ ..... 18
**ክፍል ሶስት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቦታ፣ የአስከሬን ማሳረፊያ ጉድጓድ፣ የራስጌ ምልክት እና የአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ /ዴፖ/ ስታንዳርድ ..... 24**
7. የዘላቂ ማረፊያ ቦታ አዘገጃጀት ..... 24
8. ለሙታን የሚዘጋጅ ዘላቂ ማረፊያ ጉድጓድ ስታንዳርድ ..... 24
9. በዘላቂ ማረፊያ ጉድጓድ ላይ የሚተከል የራስጌ ምልክት ግንባታ ስታንዳርድ ..... 25
10. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ/ዴፖ /Depot for skeletons/ ..... 27
11. በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ የስብስብ አስከሬን ጉድጓድ አዘገጃጀት ስታንዳርድ ..... 27
**ክፍል አራት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ የአስተዳደር ስታንዳርድ ..... 29**
12. የምድረ-ግቢው የአስተዳደር ስታንዳርድ ..... 29
12.1. አጠቃላይ መሥፈርት ..... 29
12.2. የቀብር ፍቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ አቀራረብ ..... 29

12.3.መረጃ አያያዝና አስተዳደር ............ 30
13. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቀብር ስርዓት አመዘጋገብ /Burial registers/ ............ 30
14. የአስከሬን ሳጥን ስታንዳርድ ............ 31
15. የቀብርና ሌሎች ተዛማጅ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎቶች መስጫ የስራ ሰዓት ............ 31
16. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ በቀብር ስነ-ስርዓት ላይ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና የመታሰቢያ ሥነ-ሥርዓት ............ 32
17. ቀብር አስፈጻሚዎች ............ 32
18. የአስከሬን ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ስታንዳርድ ............ 33
19. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ መድረ ግቢ ውስጥ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ስታንዳርድ ............ 33
20. የአስከሬን የማጓጓዝ ስታንዳርድ ............ 33
21. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የጽዳትና ውበት ስታንዳርድ ............ 33
21.1. የጽዳት አጠባበቅ ስታንዳርድ ............ 33
21.2. ለጽዳትና ውበት ስራዎች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ............ 34
21.3. የዘላቂ ማረፊያ እንክብካቤና በአትክልት የማስዋብ ስራ ............ 35
22. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት መጠቀሚያ ታሪፍ ............ 35
23. የሰራተኞች የግል ደህንነትና ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች /personal protective equipment/ ............ 36
23.2. የሰራተኞች ጤና እና ደህንነት ............ 36
24. ስልጠና ............ 37
25. የስራ ላይ ደህንነት ............ 37
26. የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ............ 38
ዕዝሎች ............ 39
ዕዝል አንድ፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ ውስጥ ከከተሞች ፈርጅ አንፃር ያሉትን ልዩነቶች ማሳያ/መጠቆሚያ ሠንጠረዥ፤ ............ 39
ማጣቀሻዎች ............ 50

## መግቢያ

ከተሞቻችን ጽዱ፣ ውብና ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ራዕይ በመሰነቅ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ እስካሁን በተደረገው ርብርብ ቀላል የማይባሉ የሚታዩ ውጤቶች ከመመዝገባቸው ባለፈ ፈጣን ለውጥ ጭምር ማምጣት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናና ግልጽነት የሚጎድለው ከመሆኑም በላይ ቦታዎቹ በአብዛኛው በአረንጓዴ እጽዋት ያልተሸፈኑ፣ ዲዛይን ያልወጣላቸው እና ጽዳት የጎደላቸው በመሆናቸው በከተሞች ውበት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥረዋል፡፡ በከተሞቻችን በአጠቃላይ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት አቅርቦት ተደራሽነቱና የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናው ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አገልግሎቱን ለማግኘት ነዋሪው በአማካይ ከ5 እስከ 7 ኪሎ ሜትር የሚጓዝበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በአጠቃላይ የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት አሰጣጥ ኋላቀርና የቦታ አጠቃቀሙም ስርዓት የሌለው ሆኖ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም የአካባቢ ብክለት በህዝቡ ጤና ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ፣ የህዝቡን መሠረታዊ የአገልግሎት ጥያቄና በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ያለውን ከተሜነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የፌዴራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 26 (1) (መ) እና (ከ) በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያዎችን በተገቢው ቦታ ላይ ገንብቶ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ የአስተዳደር ሥርዓቱን ለማጠናከር እንዲሁም የከተማ ነዋሪዎችም ሆኑ መንገደኞች ሳይቸገሩ ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት በተገቢው ቦታና ጊዜ እንዲያገኙና የአካባቢ ብክለት እንዲቀንስ ለማድረግ ይህንን ስታንዳርድ አዘጋጅቷል፡፡ ዓላማውም በከተሞቻችን የሚሰጠው ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ የተገልጋዮች እርካታ ከፍ እንዲል ለማድረግ ነው፡፡ በዝግጅት ሥራውም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ማሻሻል ዳይሬክቶሬትና ከአዲስ አበባ ውበትና መናፈሻ፣ ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ የተውጣጡ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

ስታንዳርዱ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ ክፍል ሁለት የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የማልማት ስታንዳርድ፣ ክፍል ሶስት የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቦታ፣ የአስክሬን ማሳረፊያ ጉድጓድ፣ የራስጌ ምልክት እና

የአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ /ዴፖ/ ስታንዳርድ፣ እንዲሁም ክፍል አራት የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአስተዳደር ስታንዳርድን አካቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

## 1. ወሰን

ይህ ሰነድ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ምድረ ግቢውን የማልማት፣ እና የምድረ ግቢው መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች እና የአስተዳደር ስታንዳርድ ያካተተ ሲሆን ስታንዳርዱም በአገሪቱ በሁሉም ከተሞች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ ስታንዳርድ ሠነድ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ከተሰጡት ትርጓሜያቸው አንጻር ብቻ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

2.1. **ዘላቂ ማረፊያ፡-** በከተማ ክልል ውስጥ ለአስከሬን ቀብር ወይም ለአጽም ማሳረፊያ ታስቦ የሚዘጋጅና ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተከለለ ቦታ ነው፤

2.2. **ማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ፡-** በከተማው ክልል ውስጥ ለአስከሬን ቀብር ወይም ለአጽም ማሳረፊያ ታስቦ በከተማው አስተዳደር የሚዘጋጅና የሚተዳደር ዘላቂ ማረፊያ ነው፤

2.3. **የአጽም የክብር ማረፊያ ወይም ዴፖ፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ በመቃብር የመቆያ ጊዜአቸውን የጨረሱ አጽሞች ተሰብስበው በክብር የሚቀመጡበት ቦታ ነው፤

2.4. **አስቀባሪ፡-** የአንድን ሰው አስከሬን ስርዓተ ቀብር ለማስፈጸም ኃላፊነት የሚወስድ የመንግስት አካል ወይም ግለሰብ ነው፤

2.5. **የመደበኛ ቀብር አገልግሎት፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለማንኛውም አስቀባሪ ወገን ወይም ዘመድ ላለው አስከሬን የሚፈጸም የቀብር አገልግሎት ነው፤

2.6. **የባይተዋር ቀብር አገልግሎት፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለማንኛውም አስቀባሪ ወገን ወይም ዘመድ ለሌለውና በመንግስት አካላት አስቀባሪነት ለሚቀርብ አስከሬን የሚፈጸም የቀብር አገልግሎት ነው፤

2.7. **ቀብር አስፈጻሚ፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለሚከናወን ስርዓተ ቀብር ጉድጓድ የማዘጋጀት፣ የመቅበር፣ የራስጌ ምልክት የመትከል ስራ የሚያከናውኑ በዘላቂ ማረፊያው የተመዘገቡና ፍቃድ የተሰጣቸው አካላት ናቸው፤

2.8. **የመቃብር ክልል፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለቀብር ብቻ የተከለለና የተዘጋጀ ስፍራ ነው፤

2.9. **የቀብር ስፍራ፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለልዩ ልዩ የእምነት ተከታዮችና ለባይተዋር ቀብር አገልግሎት ለየብቻ ተከልሎ የተዘጋጀ የአስከሬን ማሳረፊያ ቦታ ነው፤

2.10. **አስከሬን፡-** ማንኛውም የሞተ ሰው ሲሆን ሞቶ የተወለደ ልጅ አካልንም ያጠቃልላል፤

2.11. **አጽም፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በመቃብር የመቆያ ጊዜውን የጨረሰ የሰው ቅሬት ነው፤

2.12. **ቀብር፡-** አንድን አስከሬን በተዘጋጀለት ጉድጓድ ውስጥ በማሳረፍ አፈር የማልበስ ስራ ነው፤

2.13. **መቃብር፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ አንድ አስከሬን ያረፈበት ጉድጓድ ሲሆን ለጉድጓዱ የተተከለውንም የራስጌ ምልክት ወይም መለያ ድንጋይ የሚያካትት ነው፤

2.14. **የአስከሬን ሳጥን፡-** ለአስከሬን መያዣነት የሚያገለግል ከእንጨት የተሰራ ሳጥን ነው፤

2.15. **የራስጌ ምልክት:-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለሚያርፍ መደበኛ አስከሬን በመቃብሩ ራስጌ ላይ የሚተከል የምልክት ድንጋይ ነው፤

2.16. **መለያ ድንጋይ፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለባይተዋር መቃብር መለያነት እንዲያገለግል ታስቦ የሚተከል ድንጋይ ነው፤

2.17. **መለያ ኮድ፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ያረፈን አስከሬን ለመለየት በዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር የሚሰጥ ልዩ ኮድ ሆኖ ለባይተዋር ቀብር መለያ ድንጋይ ላይ፣ ለመደበኛ ቀብር በራስጌ ምልክት መሠረት ላይ የሚጻፍ ነው፤

2.18. **አስከሬን ቆፍሮ ማውጣት፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ያረፈን አስከሬን ለተለያዩ ምክንያች ማውጣት ሲያስፈልግ ከጉድጓዱ ቆፍሮ ማውጥት ነው፤

2.19. **መልሶ መቅበር፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በተለያዩ ምክንያች ተቆፍሮ የወጣን አስከሬን ወደ ጉድጓድ መልሶ በማሳረፍ አፈር የማልበስ ስራ ነው፤

2.20. **የስብስብ ቀብር አገልግሎት፡-** በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ 2 እና ከዚያ በላይ አስከሬኖችን በአንድ ጉድጓድ ውስጥ በአንድ ጊዜ የማሳረፍ አገልግሎት ነው፤

2.21. **ሜትሮፖሊስ አስተዳደር፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.22. **የሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች፡-** ከአገሪቱ ከተሞች መካከል የሜትሮፖሊስ አስተዳደርን ቀጥሎ በ2ኛ ደረጃ ያሉ ከተሞች ሲሆኑ እነዚህም ድሬደዋ፣ መቀሌ፣ ባህርዳር፣ ደሴ-ኮምቦልቻ፣ ጎንደር፣ ሐዋሳ፣ ጅማ፣ አዳማ፣ ነቀምት፣ ሮቤ፣ ሰመራ እና ጎዴ ናቸው፡፡

2.23. **ፈርጅ አንድና ቀጥሎ ያሉት ከተሞች፡-** ከአገሪቱ ከተሞች መካከል በሜትሮፖሊስ እና በሪጂፖሊስ አስተዳዳር ከተማነት ያልተካተቱ ከፈርጅ አንድ እስከ አምስት የሚፈረጁ/የተፈረጁ ከተሞች ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ

## 3. የፊትለፊት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ

### 3.1. የዘላቂ ማረፊያ ሰራተኞች የሚከተሉትን ማሟላት/ መተግበር ይኖርባቸዋል፡-

(ሀ) የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች በስራ ወቅት ማንነታቸውን የሚገልጽ የስም መለያ ባጅ በማድረግ ጽዳቱን በጠበቀ አኳኋን ለአገልግሎት ሰጪዎች የሚዘጋጀውን የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል፤

(ለ) የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ለተገልጋዮች በቀናነትና ግብረገብ በተሞላበት ሁኔታ ተገልጋዮችን ማስተናገድ ይኖርባቸዋል፤

(ሐ) የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ቢሮዎች ዘወትር ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ እስከ ቀኑ 11፡30 ክፍት ሆነው አገልግሎት ይሰጣሉ፤

### 3.2. የመረጃ ዴስክ ስታንዳርድ

(ሀ) የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ የመረጃ ዴስክ ሊኖረው ይገባል፤

(ለ) የመረጃ ዴስኩም ስፋት ቢያንስ 2 ሜትር በ 3 ሜትር መሆን አለበት፤

(ሐ) የመረጃ ዴስክ ቢያንስ 1 ሰራተኛ ሊያስተናግድ የሚችል ጠረጴዛና ወንበር ሊኖረው ይገባል፣

(መ) የመረጃ ዴስክ አቅጣጫ ለደንበኞች በቀላሉ እንዲታይ ከህንጻው መግቢያ በር ላይ መሆን ያለበት ሲሆን በተጨማሪም የመረጃ ዴስክነቱን የሚገልጽ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡

### 3.3. የተገልጋዮች የመቆያ ቦታ /waiting room/ ስታንዳርድ

የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የተገልጋዮች መቆያና መስተንግዶ ቦታ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን በሚከተሉት ስታንዳርዶች መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡-

(ሀ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ጽዱና ምቹ መሆን አለበት፤

(ለ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ተገልጋዮችን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ሆኖ የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተገልጋዮች ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፤

(ሐ) በተገልጋዮች መቆያ ቦታ ላይ ስለአገልግሎት አሰጣጡ እና ስለተገልጋዮች ግዴታ የሚያስረዱ ብሮሸሮች እና ሌሎች ጠቃሚና ወቅታዊ መረጃዎች በሚታይና ተደራሽ በሆነ ቦታ መቀመጥ/መለጠፍ አለባቸው፤

(መ) የተገልጋዮች መቆያ ቦታ ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ሲጠባበቁ የሚቀመጡበት በአንድ ጊዜ ቢያንስ 5 ተገልጋይ ሊያስቀምጡ የሚችሉ ወንበሮች ሊኖሩት ይገባል፤

(ሠ) በተገልጋዮች መቆያ ቦታ ላይ ተገልጋዮች ስለ አገልግሎት አሰጣጡ አስተያየት የሚሰጡበት መዝገብ፣ የአስተያየት መስጫ ሳጥንና እስክሪብቶ ሊቀመጥ ይገባል፤

(ረ) ዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ጫት መቃም፣ ሲጃራ ማጨስ እና ሌሎች ለህዝብ ጤና ጠንቅ የሆኑ ተግባራትን መፈጸም እንደሌለባቸው መልዕክት አስተላላፊ በራሪ ጽሑፎች /fliers/ ተዘጋጅተው ተገልጋዮች ሊያነቡት በሚችሉበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤

(ሰ) ተገልጋዮች በዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ መጣል እንደሌለባቸው፣ ማንኛውንም ዓይነት ተገቢ ያልሆኑ ጽሁፎችን መቃብር ላይ መለጠፍ እንደሌለባቸው፣ የመቃብር ስፍራዎችን እና ቁሳቁሶችን ሆን ብሎ ማበላሸትና ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሌለባቸው መልዕክት ማስተላለፊያ ብሮሸሮች ተዘጋጅተው በተገልጋዮች መቆያ ቦታ /waiting room/ መቀመጥ/በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለባቸው፤

### 3.4. አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ስታንዳርድ

(ሀ) በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የምድረ ግቢ ውስጥ የምድረ ግቢውን ልዩ ልዩ ፋሲሊቲዎችና ክፍሎች የሚያመላክቱ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች መለጠፍ ወይም መተከል አለባቸው፤

(ለ) የአቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ከብረት ሊሰሩ ይገባል፤

(ሐ) አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቱ 50 ሴ.ሜ በ 12 ሴ.ሜ መጠን ሊኖረው ይገባል፤

(መ) የአቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቱ ከምድር ቢያንስ 1.5 ሜትር ከፍ ብሎ ሊለጠፍ ወይም ሊተከል ይገባል፤

(ሠ) አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቱ ለእይታ ግልጽ የሆነ ቦታ ላይ ሊተከል ወይም ሊለጠፍ ይገባል፤

(ረ) አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቱ ላይ የሚጻፈው ጽሁፍ ጉልህና ተነባቢ መሆን አለበት፤

# 4. ዝርዝር አገልግሎቶች፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ-ሁኔታዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ

## 4.1. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የመደበኛ ቀብር አገልግሎት

4.1.1. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የመደበኛ ቀብር አገልግሎት ለማግኘት በተገልጋይ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፤

(ሀ) አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ[1]-001 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) የአስቀባሪውን ማንነትና አድራሻውን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ፤

(ሐ) ከተቻለ የሟችን ማንነትና ይኖርበት የነበረውን አድራሻ የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ፤

(መ) ከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤

4.1.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.1.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት የመደበኛ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፦ ለአንድ የመደበኛ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 3 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 1 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 1**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የተገልጋዩ የመደበኛ ዘላቂ ማረፊያ ጥያቄ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ማስሞላትና መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | የቀብር ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት ተለክቶ ለቆፋሪዎች ከነሽንሻኖ ቁጥሩ ማስረከብ | 30 ደቂቃ |
| 3 | የቀብር ጉድጓድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስቆፍሮ ማዘጋጀት | 2 ሰዓት |
| 4 | ቀብር መፈጸም[2] | 30 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 3 ሰዓት ከ20 ደቂቃ |

[1] ዘማ፡- ዘላቂ ማረፊያ

[2] ለቀብር መፈጸም የተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ የሃይማኖትና የባህል ስነስርዓቶችን ለመከወን የሚወስደውን ጊዜ አያካትትም፡፡

(ለ) መጠን፡- ለአንድ አስከሬን ቀብር ለመፈጸም፤

(ሐ) ጥራት፡- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የጉድጓድ ዝግጅትና ቀብር አገልግሎት ከተፈጸመ፤

(መ) ወጪ፡- የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሰረት የአገልግሎትና የሰራተኛ ጉልበት ክፍያ፤

## 4.2. የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ መቃብር የራስጌ ምልክት የመትከል አገልግሎት

### 4.2.1. በማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ መቃብር የራስጌ ምልክት የመትከል አገልግሎት ለማግኘት በተገልጋይ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፤

በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.1.1 የተቀመጡት ቅድመሁኔታዎች ለዚህም አገልግሎት መሟላት አለባቸው፤

4.2.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.1.1. የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት የዘላቂ ማረፊያ የራስጌ ምልክት የመትከል አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፡- አንድ የዘላቂ ማረፊያ የራስጌ ምልክት የመትከል አገልግሎት ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 4 ቀን ከ3 ሰዓት ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 2 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 2**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የተገልጋዩ የዘላቂ ማረፊያ የራስጌ ምልክት እንዲተከል መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001[3] ማስሞላትና መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | የራስጌ ምልክቱ ላይ የሚሰፍረውን ጽሁፍና ምልክት ከሟች ወገን በጽሁፍ መቀበል | 5 ደቂቃ |
| 3 | የራስጌ ምልክትና መሰረቱን ማዘጋጀት | 4 ቀን |
| 4 | የራስጌ ምልክት ተከላ | 2 ሰዓት |
| 5 | የመቃብር አካባቢ ጽዳት | 35 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 4 ቀን ከ3 ሰዓት |

(ለ) መጠን፡- አንድ የመቃብር የራስጌ ምልክት፤

[3] ቀብር ለመፈጸምና የራስጌ ምልክት እንዲተከል የሚጠየቅበት ቅጽ አንድ ነው (ቅጽ 001)

(ሐ) ጥራት፦ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የራስጌ ምልክት ከነመሰረቱ ተዘጋጅቶ ከተተከለ፤

(መ) ወጪ፦ የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሰረት የሰራተኛ ጉልበት ክፍያ፤

## 4.3. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የባይተዋር ቀብር አገልግሎት ስታንዳርድ

4.3.1. የባይተዋር ቀብር አገልግሎት ጠያቂ ተገልጋይ ማሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፤

(ሀ) የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) የጤና ተቋማት ምርመራን መነሻ በማድረግ ከፖሊስ አካል እንዲቀበር የታዘዘበት ህጋዊ ደብዳቤ፤

(ሐ) ከተቻለ የሟችን ማንነትና ይኖርበት የነበረውን አድራሻ የሚገልጽ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

4.3.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.3.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት ባይተዋር ቀብር አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፦ አንድ የባይተዋር ቀብር አገልግሎት ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 3 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 3 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 3**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | አስቀባሪውን የባይተዋር ቀብር አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ማስሞላትና ከነሸኚ ደብዳቤው መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | አስከሬኑን ካመጣው አካል መረከብ | 20 ደቂቃ |
| 3 | የቀብር ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት ለክቶ ለቆፋሪዎች ከነሽንሻኖ ቁጥሩ ማስረከብ | 30 ደቂቃ |
| 4 | የቀብር ጉድጓድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስቆፍሮ ማዘጋጀት | 2 ሰዓት |
| 5 | ቀብር መፈጸም | 30 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 3 ሰዓት ከ40 ደቂቃ |

(ለ) መጠን፦ ለአንድ የባይተዋር አስከሬን ቀብር ለመፈጸም፤

(ሐ) ጥራት፡-በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የጉድጓድ ዝግጅትና ቀብር አገልግሎት ከተፈጸመ፤

(መ) ወጪ፡- በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን፤

## 4.4. የስብስብ ቀብር አገልግሎት ስታንዳርድ

4.4.1. የስብስብ ቀብር አገልግሎት ጠያቂ ተገልጋይ ማሟላት ያለበት ቅድመ-ሁኔታዎች

(ሀ) የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) ስብስቡ ማንነታቸውን መለየት ያልተቻለ ከሆነ የጤና ተቋማት ምርመራን መነሻ በማድረግ ከፖሊስ አካል እንዲቀበር የታዘዘበት ህጋዊ ደብዳቤ ማቅረብ፤

(ሐ) ስብስቡ ማንነታቸውን መለየት የሚቻል ከሆነ በዚህ ስታንዳርድ ለማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የመደበኛ ቀብር አገልግሎት የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት፤

4.4.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.4.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት የስብስብ ቀብር አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፡- አንድ የስብስብ ቀብር /ከ2 እስከ 10 አስከሬን/ አገልግሎት ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ ከ6፡30 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 3 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ4**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | ማንነታቸው ባልተለየ የስብስብ ቀብር አስቀባሪውን አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ማስሞላትና ከነሸኚ ደብዳቤው መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | አስከሬኑን ካመጣው አካል መረከብ | ከ40 እስከ 60 ደቂቃ |
| 2 | የቀብር ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት ለክቶ ለቆፋሪዎች ከነሽንሻኖ ቁጥሩ ማስረከብ | 30 ደቂቃ |
| 3 | የቀብር ጉድጓድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስቆፍሮ ማዘጋጀት | ከ4 እስከ 6 ሰዓት |
| 4 | ቀብር መፈጸም | ከ1 እስከ 2 ሰዓት |
| | **ድምር** | ከ6፡30 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት |

(ለ) መጠን፡- የአንድ ስብስብ /ከ2 እስከ 10 አስከሬን/ ቀብር መፈጸም፤

(ሐ) ጥራት፡-በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የጉድጓድ ዝግጅትና ቀብር አገልግሎት ከተፈጸመ፤

(መ) ወጪ፡- ስብስቡ ማንነታቸው ያልተለየ ከሆነ በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን ይሆናል፤ ስብስቡ ማንነታቸው የተለዩ ከሆነ አስቀባሪው ከተማ አስተዳደሩ በሚያወጣው ታሪፍ መሰረት ክፍያ ይፈጽማል፤

## 4.5. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያው ምድረግቢ ውስጥ ስርዓተ ቀብር ስለመፈጸሙ ማስረጃ የመስጠት አገልግሎት

4.5.1. ማስረጃ ጠያቂ ተገልጋይ ማሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፡-

(ሀ) የአገልግሎት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ ዘማ-002 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) ማስረጃ ጠያቂዎቹ የሟች እናት ወይም አባት ወይም ባል ወይም ሚስት ወይም ከሟች የተወለዱ ልጆች ወይም ሞግዚት ወይም ህጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ማረጋገጫ ዋናውንና አንድ ፎቶኮፒ ማቅረብ፤

(ሐ) የጠያቂው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ወይም ሊሴፓሴ ዋናውና አንድ ኮፒ ማቅረብ፤

(መ) ከፖሊስና ከፍ/ቤት ለሚቀርብ የማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ከጠያቂው አካል የተጻፈ ህጋዊ ደብዳቤ ማቅረብ፤

(ሠ) ጥያቄው በውክልና ከሆነ በውክልናው ላይ የሞት ማስረጃ እንዲሰጥለት የተገለጸበት ውክልና ማቅረብ፤

(ረ) ጠያቂው ኤምባሲ ከሆነ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ከኤምባሲው የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ፤

(ሰ) ከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤

4.5.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.5.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ቀብር ስለመፈጸሙ ማስረጃ ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፡- ለአንድ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለተቀበረ ሟች ማስረጃ የመስጠት አገልግሎት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 42 ደቂቃ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 5 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ 5

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የተገልጋዩ በዘላቂ ማረፊያው ለመቀበሩ ማስረጃ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-002 ማስሞላትና መቀበል | 5 ደቂቃ |
| 2 | መረጃን ማጣራት | 20 ደቂቃ |
| 3 | የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል | 5 ደቂቃ |
| 4 | ማስረጃ ዝግጅት | 10 ደቂቃ |
| 5 | ማስረጃውን አስፈርሞ መስጠት | 2 ደቂቃ |
| | ድምር | 42 ደቂቃ |

(ለ) መጠን፡- አንድ የተዘጋጀ ማስረጃ፤

(ሐ) ጥራት፡-ለአያያዝ ምቹ፣ ጠንካራ፣ ጽሁፎቹ በቀላሉ የማይበላሹ፣ ስርዝ ድልዝ የሌለው የተሟላ መረጃ የያዘ

(መ) ወጪ፡- የከተማ አስተዳደሩ በወሰነው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ

## 4.6. ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት

4.6.1. ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ ለማግኘት ተገልጋይ ማሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፤

(ሀ) አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-004 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) ዝውውር ጠያቂዎቹ የሟች እናት ወይም አባት ወይም ባል ወይም ሚስት ወይም ከሟች የተወለዱ ልጆች ወይም ሞግዚት ወይም ህጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ማረጋገጫ ዋናውንና አንድ ፎቶኮፒ ማቅረብ፤

(ሐ) የዝውውር ጠያቂው የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ወይም ሊሴፓሴ ዋናውና አንድ ኮፒ፤

(መ) ጥያቄው በውክልና ከሆነ በውክልናው ላይ የአስከሬን/አጽም የማዘዋወሪያ ፈቃድ እንዲሰጥለት የተገለጸበት ውክልና ማቅረብ፤

(ሠ) ዝውውር ጠያቂው ኤምባሲ ከሆነ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ከኤምባሲው የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ፤

(ረ) ከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤

4.6.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.6.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፡- ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አንድ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 4 ሰዓት ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 6 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 6**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የተገልጋዩ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-004 ማስሞላትና መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል | 10 ደቂቃ |
| 3 | የማዘዋወር ፈቃዱንና አስከሬኑ ሲቀበር የተደራጀውን ሙሉ መረጃ መስጠት | 20 ደቂቃ |
| 4 | የቀብር ቦታውን መለየት | 30 ደቂቃ |
| 5 | አስከሬን/አጽም ቆፍሮ ማውጣት | 2 ሰዓት |
| 6 | አስከሬኑን/አጽሙን ለማጓጓዝ በሚያመች መልክ ማዘጋጀት | 30 ደቂቃ |
| 7 | አስከሬኑን ወይም አጽሙን አስፈርሞ ማስረከብ | 10 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 4 ሰዓት |

(ለ) መጠን፡- አንድ ወደ ሌላ አድራሻ የሚዘዋወር አስከሬን ወይም አጽም፤

(ሐ) ጥራት፡- አስክሬኑ ወይም አጽሙ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለማጓጓዝ በሚያመች መልክ ከተዘጋጀ፤

(መ) ወጪ፡- የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ፤

## 4.7. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ለቁሳቁስ አቅርቦት፣ ለማህበራትና ለግል ድርጅቶች ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት

4.7.1. ፈቃድ ለማግኘት በተገልጋይ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፤

(ሀ) አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-006 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) ለስራው ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፤

(ሐ) ከአደራጁ አካል የስራ ፈቃድ ማቅረብ፤

(መ) የንግድ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ ማቅረብ፤

(ሠ) ከዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ጋር የስራ ውል መዋዋል፤

(ረ) ከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፤

4.7.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.7.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፦ ለአንድ የመደበኛ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ለመስጠት የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 7 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 7**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የተገልጋዩ የስራና የቁሳቁስ አቅርቦት ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-006 ማስሞላትና መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል | 10 ደቂቃ |
| 3 | ማስረጃዎችን ማረጋገጥ | 30 ደቂቃ |
| 4 | ውል መዋዋል | 1 ሰዓት |
| 5 | ፈቃድ መስጠት | 10 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ |

(ለ) መጠን፦ ለአንድ ማህበር ወይም የግል ድርጅት የተሰጠ የስራና የቁሳቁስ አቅርቦት ፈቃድ፤

(ሐ) ጥራት፦ ለአያያዝ ምቹ፣ ጠንካራ፣ ጽሁፎቹ በቀላሉ የማይበላሹ፣ ስርዝ ድልዝ የሌለው የተሟላ መረጃ የያዘ ፈቃድ

(መ) ወጪ፦ የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ፤

## 4.8. በዝወውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የመጣ አስከሬን የመቅበር ወይም አጽም የማሳረፍ አገልግሎት

4.8.1. በዝወውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የመጣ አስከሬን ለመቅበር ወይም አጽም ለማሳረፍ በተገልጋይ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

(ሀ) አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) የአስቀባሪውን ወይም አጽም አሳራፊውን ማንነትና አድራሻውን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ፤

(ሐ) ቀደም ሲል ከነበረበት ዘላቂ ማረፊያ የተሰጠው የአስከሬን ወይም የአጽም እና ማዘዋወሪያ ፈቃድ ማቅረብ፤

(መ) ቀደም ሲል ከነበረበት ዘላቂ ማረፊያ የተመዘገበው የአስከሬኑ ወይም የአጽሙ ሙሉ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

(ሠ) የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፤

4.8.2. ተገልጋዩ በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 4.8.1 የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ካሟላ በሚከተሉት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች መሰረት አንድ በዝውውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የመጣ አስከሬን የመቅበር ወይም አጽም የማሳረፍ አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) ጊዜ፡- አንድ ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የተዛወረ አስከሬን ቀብር ወይም አጽም ማሳረፍ የሚወስደው አጠቃላይ ጊዜ 3 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 8 በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 8**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ቅደም ተከተል | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | ተገልጋዩ በዝወውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የመጣ አስከሬን ወይም አጽም ለማሳረፍ የመደበኛ ዘላቂ ማረፊያ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ማስሞላትና መቀበል | 20 ደቂቃ |
| 2 | የቀረበውን ማዘዋወሪያ ፈቃድና አስከሬኑን ወይም አጽሙን ሙሉ መረጃ ማጣራትና መመዝገብ | 20 ደቂቃ |
| 3 | የቀብር ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት ተለክቶ ለቆፋሪዎች ከነሸንሻኖ ቁጥሩ ማስረከብ | 30 ደቂቃ |
| 4 | የቀብር ጉድጓድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አስቆፍሮ ማዘጋጀት | 2 ሰዓት |
| 5 | አስከሬን ከሆነ ቀብር መፈጸም ወይም አጽም ከሆነ በክብር ማሳረፊያ ዴፖ ማሳረፍ[4] | 30 ደቂቃ |
| | **ድምር** | 3 ሰዓት ከ40 ደቂቃ |

[4] ለአስከሬን ቀብር ወይም ለአጽም ማሳረፍ የተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ የሃይማኖትና የባህል ስነስርዓቶችን ለመከወን የሚወስደውን ጊዜ አያካትትም፡፡

(ለ) መጠን፦ አንድ ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የተዛወረ አስከሬን መቅበር ወይም አጽም ማሳረፍ፤

(ሐ) ጥራት፦ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የጉድጓድ ዝግጅትና ቀብር ወይም አጽም በክብር ማሳረፊያ ዴፖ ማሳረፍ አገልግሎት ከተፈጸመ፤

(መ) ወጪ፦ የከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ፤

## 4.9. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ ማውጣትና መልሶ መቅበር /exhumation and reburial/

4.9.1. ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማራፊያ አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ ማውጣት የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-

(ሀ) አስከሬኑ ከተቀበረ ቢያንስ 7 ዓመት ያለፈው ሆኖ አጽሙ ወደ ክብር ማሳረፊያ ዴፖ መዘዋወር ሲኖርበት፤

(ለ) ለተለያዩ ምርመራዎች አስከሬኑን ማውጣት በሚፈለግበት ጊዜ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ ይሆናል፤

(ሐ) አስከሬን 7 ዓመት ሳይሞላው ተቆፍሮ ሊወጣ የሚችለው የሟች ዘመዶች ህጋዊ ባለመብት መሆናቸውን የሚገልጽ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዘው ሲቀርቡ ብቻ ነው፤

(መ) ዘላቂ ማረፊያው በልዩ ምክንያቶች አስከሬኑን ከተቀበረበት ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፤

4.9.2. ማንኛውም አስከሬን ቆፍሮ ወይም አስቆፍሮ የማውጣት ስርዓት የሚከናወነው የሟች ዘመዶች ወይም አስክሬኑን ያስቀበረው አካል አግባብ ባለው መንገድ ከ7 ቀን በፊት ከተገለጸላቸው በኋላ ነው፤

4.9.3. ማንኛውም አስከሬን ቆፍሮ ወይም አስቆፍሮ የማውጣት ስርዓት የሚከናወነው የከተማው ፖሊስ በተገኘበት መሆን አለበት፤

4.9.4. አስከሬን ለማውጣት የሚያስፈልገውን የማስቆፈርያ ወጪ የሚሸፍነው የማስቆፈር ስልጣን ተሰቶት አስቆፍሮ አስከሬኑን የሚያስወጣው አካል ነው፤

4.9.5. አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ የማውጣት አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዩ ቅጽ ዘማ-004 ሞልቶ ከ2 ቀን በፊት ለዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

4.9.6. አንድ በባይተዋርነት የተቀበረ አስከሬን ወገኖቹ ወይም ዘመዶቹ አስቆፍረው ማውጣት በሚፈልጉበት ጊዜ የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ለቀብሩ ያወጣውን ወጪ ጨምረው መክፈል ይኖርባቸዋል፤

4.9.7. አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ እንዲያወጣ የተፈቀደለት አካል የአስከሬኑን መያዣና ማጓጓዣ ማቅረብ ይኖርበታል፤

4.9.8. አስከሬን ወይም አጽም ቆፍሮ እንዲያወጣ ስልጣን የተሰጠው አካል አስከሬኑና መቃብሩ ሽታና በሽታ እንዳያመጣ የሽታ ማስወገጃ እና ተህዋስያን ማጥፊያ መጠቀም አለበት፤

## 5. መልሶ መቅበር /Reburial by Council/

5.1. አንድ አስክሬን ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ሊቀበር የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሆናል፡-

(ሀ) አስከሬኑ መጀመሪያ ሲቀበር በዚህ ስታንዳርድ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች በጣሰ ሁኔታ የተቀበረ መሆኑ በዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ሲረጋገጥ፤

(ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለልዩ ልዩ ምርመራዎች ተቆፍሮ የወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

(ሐ) በልዩ ምክንያቶች ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ አስከሬኑን ቆፍሮ አውጥቶ መቅበር ሲፈልግ፤

5.2. በመልሶ መቅበር ጊዜ የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ተገቢውን የሚቹን ሃይማኖታዊ ይሁን ተጓዳኝ የቀብር ስርዓት መፈጸም ይገባዋል፤

5.3. በዝውውር ከሌላ ዘላቂ ማረፊያ የሚመጣ አጽም /7 ዓመትና ከዚያ በላይ እድሜ ያስቆጠረ/ ሊያርፍ የሚችለው በክብር ማሳረፊያ ዴፖ ውስጥ ብቻ ነው፤

# ክፍል ሁለት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የማልማት ስታንዳርድ

## 6. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ልማት ስታንዳርድ

### 6.1. የቦታ መረጣ /site selection/ ስታንዳርድ

የዘላቂ ማረፊያ ለመገንባት የቦታ መረጣ በሚከተለው ስታንዳርድ መሠረት መፈጸም አለበት፤

(ሀ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የሚመረጥ ቦታ ከአካባቢው የመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር የተጣጣመና በከተማው ፕላን የተፈቀደ መሆን ይገባዋል፤

(ለ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ የሚመረጥ ቦታ ብክለትን ለመከላከል የወጡ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን የተከተለ መሆን ይገባዋል፤

(ሐ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ግንባታ የሚመረጥ ቦታ መሰረተ ልማት /ማለትም ውሃ፣ መብራት፣ መንገድና ተፋሰስ ወዘተ/ የተዘረጋለት መሆን ይገባዋል፤

(መ) ለማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ግንባታ የተመረጠ ቦታ ሳይት ፕላንና የይዞታ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፤

(ሠ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከተው አካል የግንባታ ፍቃድ ማግኘት አለበት፤

(ረ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ለጎርፍ እና ውሃ ለማቆር ተጋላጭ በሆነ ቦታ መገንባት የለበትም፤

(ሰ) የከተማ አስተዳደሩ ለማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቦታ ስፋት ሲወስን የከተማውን ፈጣን የህዝብ ዕድገት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ቦታውም በህዝብ መነፈሻነት ጭምር የሚያገለግል እንደሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት በቂ የሆነ ቦታ ማዘጋጀት አለበት፤

(ሸ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ቦታ ሲመረጥ የህዝብ ስርጭትንና ስነ ምድራዊ አቀማመጥን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

(ቀ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ቦታ ሲመረጥ ስነ ምድራዊ አቀማመጥን ያገናዘበ ሆኖ የተዳፋት መጠኑ ከ15 ዲግሪ በላይ መሆን የለበትም፤

(በ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ቦታ ሲመረጥ ከህዝብ መኖሪያ፣ ከማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት (ት/ቤት፣ ሆስፒታል፣ ከመጠጥ ውሃና ጸበል ምንጮች ቢያንስ 3 ኪ.ሜ. መራቅ ይኖርበታል)

(ተ) ማንኛውም ማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ቦታ ሲመረጥ አፈሩ አሸዋማ መሆን የለበትም፤

(ቸ) አንድ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ከአጠቃላይ ስፋቱ 70 በመቶው ለመቃብር ክልል እንዲሁም 30 በመቶው ለመሰረተ ልማት እና ለልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ፋሲሊቲዎች መዋል አለበት፤

## 6.2. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የምድረ ግቢ መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች/ ስታንዳርድ

6.2.1. ማንኛውም የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የምድረ ግቢው የቦታ አጠቃቀም ዲዛይን ሊዘጋጅለት ይገባል፤

6.2.2. የማንኛውም የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ የቦታ አጠቃቀም ዲዛይን ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ማካተት ይገባዋል፤

(ሀ) የዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ አጥር እና የመግቢያ በር፤

(ለ) የሰንደቅ አላማ ህዝባዊ አደባባይ፤

(ሐ) የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፤

(መ) የአስተዳደር ህንጻ፤

(ሠ) የህዝብ መጸዳጃ፤

(ረ) የመኪና ማቆሚያ ቦታ፤

(ሰ) የአስከሬን ማሳረፊያና የማሳረጊያ ስፍራ፤

(ሸ) የአረንጓዴ መሰረተልማት፤

(ቀ) የመቃብር ክልል፤

## 6.3. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ አጥርና የመግቢያ በር ስታንዳርድ

### 6.3.1. የአጥር ስታንዳርድ

የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ዙሪያው አጥር ሊኖረው ይገባል፤ አጥርም የሚከተሉትን ስታንዳርዶች ማሟላት አለበት፡-

(ሀ) በሜትሮፖሊስና በሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች አጥሩ ከመሬት 1 ሜትር ከፍታ በግምብ የተሰራ ሆኖ በግንቡ ላይ 1 ሜትር ከፍታ ግቢውን ውስጡን ማየት በሚያስችልና ሰውንና እንስሳትን በማያሾልክ ርቀት በብረት ፍርግር መታጠር ያለበት ሲሆን፤ በፈርጅ አንድና ቀጥሎ ባሉት ከተሞች ከመሬት 2 ሜትር ከፍታ ቋሚው ብረት ሆኖ ሰውንና እንስሳትን በማያሾልክ ሁኔታ በአጥር ሽቦ መታጠር አለበት፡፡

(ለ) በአጥሩ ዙሪያ በየተወሰነ ርቀት የጥበቃ ማማ ሊሰራለት ይገባል፤ ማማውም ከመሬት 3.5 ሜትር ከፍ ብሎ መገንባት አለበት፤

(ሐ) በሜትሮፖሊስና በሪጂዮፖሊሰ አስተዳደር ከተሞች በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ዋና መግቢያ በር ላይ፣ ጥበቃ ማማ ባለበት አካባቢ፣ በመንገዶች ዳርቻ እና በመቃብር ስፍራዎች መብራት መገጠም ያለበት ሲሆን በፈርጅ አንድና ቀጥሎ ባሉት ከተሞች እንደአስፈላጊነቱ መግጠም ይቻላል፡፡

6.3.2. **የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ዋና መግቢያ በር ስታንዳርድ**

(ሀ) የመግቢያው የተጣራ የበር ስፋት ቢያንስ 6 ሜትር መሆን አለበት፤

(ለ) የመግቢያ በሩ ቁመት ከአጥሩ ቁመት ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፤

(ሐ) የዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ መሆኑን የሚገልጽ ስሙን የያዘ ጽሁፍ ሊኖረው ይገባል፤ የጽሁፉ መጠን ከርቀት በቀላሉ ሊታይ በሚችል ደረጃ መሆን አለበት፤ የዘላቂ ማረፊያ ስም የሚያርፍበት ሰሌዳ ቁመቱ 96 ኢንች፤ እንዲሁም ወርዱ 24 ኢንች መሆን አለበት፤ ጽሁፉ በምሽት በግልጽ እንዲነበብ መብራት ሊገጠምለት (በሜትሮፖሊስ አስተዳደር) ይገባል፤ በሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች ቢገጠም ይመረጣል፡፡

(ሠ) በሩ ከብረት ሊሰራ ይገባል፤

(ረ) ዋናው በር ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና ምንም ዓይነት መሰናክል የማይፈጥር ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

(ሰ) ዋናው በር መቆለፊያ ሊዘጋጅለት ይገባል፤

(ሸ) የዘላቂ ማረፊያ መግቢያ አካባቢ ለልዩ ልዩ መረጃዎች መለጠፊያ የሚያገለግል የማስታወቂያ ሰሌዳ መኖር አለበት፤

### 6.3.3. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የሰንደቅ አላማ ህዝባዊ አደባባይ ስታንዳርድ

(ሀ) አደባባዩ ከዋናው በር ከ20 እስከ 30 ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ የሚዘጋጅ ይሆናል፤

(ለ) አደባባዩ ሰንደቅ አላማ ቦታ ሊዘጋጅለት ይገባል፤

(ሐ) ሰንደቅ ዓላማ የሚተከልበት ቦታ ዲያሜትሩ ቢያንስ 2 ሜትር ሆኖ ከፍታው ከ60 እስከ 70 ሳ.ሜ መሆን ይገባዋል፤

(መ) ሰንደቅ ዓላማው የሚተከልበት ስፍራ በተለያዩ መዋቢያዎች /ሳር፣ አበባና ቅርጻቅርጾች/ መዋብ አለበት፤

(ሠ) ሰንደቅ አላማ በቀብር ወቅት ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ መደረግ አለበት፤

## 6.4. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የውስጥ ለውስጥ መንገድና የጎርፍ መውረጃ ቦይ ስታንዳርድ

(ሀ) ዘላቂ ማረፊያው ቢያንስ ከ7 እስከ 8 ሜትር ስፋት ያለው ከዋናው መግቢያ እስከ ትይዩው አጥር ድረስ የሚዘልቅ ዋና መንገድ መዘርጋት አለበት፤

(ለ) ከዋናው መንገድ እየተገነጠሉ ወደ የመቃብር ስፍራዎችና ወደ አስተዳደር ህንጻዎች የሚያመሩ ቢያንስ ከ5.5 እስከ 6 ሜትር ስፋት ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፤

(ሐ) ከሁለተኛ ደረጃ መንገዶች ተገንጥለው ወደ መቃብር ጉድጓዶች የሚያደርሱ ቢያንስ 2 ሜትር ስፋት ያላቸው የእግረኛ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፤

(መ) የሚገነቡት መንገዶች በሙሉ ጠርዝ እና የእግረኛ መንገድ /rights of way/ ሊሰራላቸው ይገባል፤

(ሠ) የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ከዘላቂ ማረፊያ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጋርና ብቻውን ሊሰራ የሚገባ ሲሆን በአጠቃላይ የምድረ ግቢውን እና የአካባቢውን የውሃ ተፋሰስ ባገናዘበ መልክ ዲዛይኑ በባለሙያ መጠናትና መዘጋጀት ይገባዋል፤

## 6.5. የአስተዳደር ህንጻ ይዘት ስታንዳርድ

በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለአስተዳደር አገልግሎት የሚገነባው ህንጻ የሚከተሉትን ማካተት ይገባዋል፡-

(ሀ) የተቋሙ የአስተዳደርና የባለሙያዎች ቢሮ፤

(ለ) የመረጃ ዴስክ እና የደንበኛ መቆያ ቦታ፤

(ሐ) የጉልበት ሰራተኞች ማረፊያና ልብስ መቀየሪያ፤

(መ) መታጠቢያና መጸዳጃ፤

(ሠ) የሰራተኛ ክበብ /cafeteria/፤

(ረ) የቁሳቁስ ማስቀመጫ ስቶር /store/፤

6.5.1. **የህዝብ መጸዳጃ ቤት ስታንዳርድ**

በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለተገልጋዮች መጸዳጃ ቤት መገንባት ያለበት ሲሆን ይህም በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጸድቆ በወጣው የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠያ የአገልግሎት፣ የማኔጅመንት እና የህንጻው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ ቁጥር ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር 28፡2007 መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፤

6.5.2. **የተሽከርካሪ ማቆሚያ /parking/ ስታንዳርድ**

ሀ/ የሰራተኞች የተሽከርካሪ ማቆሚያ ከአስተዳደር ህንጻው አቅራቢያ ሊዘጋጅ ይገባዋል፤

ለ/ ለተገልጋዮች ተሽከርካሪ ማቆሚያ ከዋናው መግቢያ በር ሳይርቅ ቢያንስ 50 ተሽከርካሪዎችን ሊያስተናግድ በሚችል ሁኔታ ሊዘጋጅ ይገባል፤

6.5.3. **በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአስከሬን ማሳረፊያና የማሳረጊያ ስፍራ ስታንዳርድ**

(ሀ) የአስከሬን ማሳረፊያው ከምድር 1 ሜትር ከፍ ተብሎ የሚዘጋጅ ሲሆን መጠኑ ቢያንስ 1.5 ሜትር በ2.2 ሜትር መሆን አለበት፤

(ለ) የአስከሬን ማሳረፊያ ቦታውም ለጸሃይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ ሊገነባለት ይገባል፤

(ሐ) በሜትሮፖሊስና በሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች ከአስከሬኑ ማሳረፊያ ፊትለፊት የሀዘንተኞች እና የቀባሪዎች ማሳረጊያና ማረፊያ ቦታ የሚኖረው ሲሆን ይህም ቦታ ለፀሐይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ እና ለማረፊያ የሚሆን መቀመጫ ሊዘጋጅለት ይገባል፤ ነገር ግን በፈርጅ አንድና ቀጥሎ ባሉት ከተሞችም ለፀሐይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ እና ለማረፊያ የሚሆን መቀመጫ ቢዘጋጅ ይመረጣል፡፡

6.5.4. **የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አረንጓዴ መሠረተ-ልማት ስታንዳርድ**

(ሀ) የዘላቂ ማረፍያ ግቢ ውስጥ በዲዛይን መሰረት ለተለያዩ አገልግሎቶች ከተያዙት ቦታዎች ውጭ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች ሁሉ በአረንጓዴ ዕጽዋት መሸፈን አለባቸው፤

(ለ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች ግራና ቀኝ በየ5 ሜትሩ የጥላና የውበት ዛፎች መተከል አለባቸው፤

(ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ለአረንጓዴ ልማት የሚተከሉት ዕጽዋት በሚዘጋጀው የላንድስኬፕ ጥናት መሰረት የሚመረጡ ሆኖ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

- ዕይታን የማይጋርዱ፤
- ውበት የሚፈጥሩ፤
- ስራቸው በመቃብርና በግንባታዎች ላይ ጉዳት የማያስከትሉ፤
- በርጥበትና ጥላ የተነሳ በመቃብርና ግንባታዎች ላይ የመበስበስና የመሰነጣጠቅ
- የሚተከሉት ዕጽዋት አገር በቀል ቢሆኑ ይመረጣል፤

(መ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ለጎብኝዎችና እንግዶች ማረፊያ የሚሆን ከእንጨት ወይም ከኮንክሪት የተሰሩ ወንበሮች መዘጋጀት አለባቸው፤

(ሠ) የሚተከሉት እጽዋት ስብጥር ትልልቅ የጥላ ዛፎችን፣ የውበት ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችን እና ለንፋስ መከለያነት የሚያገለግሉ ተክሎችን ማካተት አለበት፤

(ረ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሳር፣ ቅጠላ ቅጠሎች፣ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች በየወቅቱ መታጨድና መከርከም አለባቸው፤

(ሰ) ዛፎችንና ቁጥቋጦዎች ለመቃብርና ለአስተዳደር ህንጻው ጉዳት ሊያመጡ በሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ወይም የዘላቂ ማረፊያውን ውበት የሚያጎድፉ ሆነው ሲገኙ መወገድ አለባቸው፤

(ሸ) በመቃብር ቦታዎች ለመታሰቢያ የተቀመጡ አበባዎች ውበታቸውን ከጨረሱ በኋላ መወገድ አለባቸው፤

### 6.5.5. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ ውስጥ የመቀመጫዎች ስታንዳርድ

6.5.5.1. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለአስቀባሪዎችና ለጎብኝዎች ምቹ የሆኑ መቀመጫዎች ተዘጋጅተው በተመረጡ ቦታዎች /በመንገዶች ዳርቻ፣ በአስተዳደርና ልዩ ልዩ ህንጻዎች ዙሪያ በተክሎች የለሙ ቦታዎች ውስጥ ወዘተ/

ሊቀመጡ ይገባል፤ መቀመጫዎቹም የሚከተሉትን ስታንዳርዶች ያሟሉ መሆን አለባቸው፡-

(ሀ) በሜትሮፖሊስና በሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች ከኮንክሪት ወይም ከብረት ሊሰሩ ይገባል፤ ነገር ግን በፈርጅ አንድና ቀጥሎ ባሉት ከተሞች ከኮንክሪት ወይም ከብረት ወይም ከእንጨት ሊሰሩ ይገባል፤

(ለ) የአንድ መቀመጫ ወንበር ርዝመት 1.2 ሜትር፣ ቁመት 50 ሴ.ሜ እና ስፋት 40 ሴ.ሜ. መሆን አለበት፤

(ሐ) የጀርባ መደገፊያው ቁመት ከመቀመጫው ከ50 ሴ.ሜ ማነስ የለበትም፤

# ክፍል ሶስት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቦታ፣ የአስክሬን ማሳረፊያ ጉድጓድ፣ የራስጌ ምልክት እና የአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ /ዴፖ/ ስታንዳርድ

## 7. የዘላቂ ማረፊያ ቦታ አዘገጃጀት

(ሀ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በዲዛይን መሰረት ለመቃብርነት የተመረጠው ስፍራ ተመንጥሮ እና ተጠርጎ መደልደል አለበት፤

(ለ) ለየእምነቱ ተከታዮች እና ለባይታወር ቀብር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ቦታ ተከልሎ የቀብር ስፍራ መከፋፈል አለበት፤ ተከልሎ የተከፋፈለውም የቀብር ስፍራ በቀብር ልክ ተሸንሽኖ መለያ ኮድ ሊሰጠው ይገባል፤

(ሐ) መለያ ኮዱም መቃብሩ በየትኛው የቀብር ስፍራ እንደሚገኝ፣ በቀብር ስፍራው ውስጥ በየትኛው ረድፍና /column/ ተርታ /row/ ላይ እንዳረፈ የሚያመለክት መሆን አለበት፤

(መ) የተከፋፈለው ቦታ ለየትኛው እምነት ተከታዮች እንደተመደበ በግልጽ የሚያሳይ ምልክት ሊደረግበት ይገባል፤

(ሠ) ለየእምነት ተከታዮቹ የተከፋፈለው መሬት ለአንድ ሰው የቀብር ጉድጓድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተሸንሽኖ መቀመጥ ይኖርበታል፤ ይህ ሽንሻኖ በየመቃብር ጉድጓዶቹ በአራቱም መዓዘን መለያ የሚሆን በስታንዳርድ የተቀመጠውን መለያ የሚያካትት ይሆናል፤

## 8. ለሙታን የሚዘጋጅ ዘላቂ ማረፊያ ጉድጓድ ስታንዳርድ

(ሀ) የአንድ የአዋቂ አስከሬን ማረፊያ ጉድጓድ ርዝመቱ ከስር 2.4 ሜትር ከጉድጓዱ አፍ ላይ 2.5 ሜትር፣ ስፋቱ ከስር 0.9 ሜትርና ከጉድጓዱ አፍ ላይ 1 ሜትር፣ ጥልቀቱም 2 ሜትር መሆን አለበት፤

(ለ) የአዋቂ አስከሬን ካረፈ በኋላ ከሳጥን በላይ ቢያንስ 1.2 ሜትር ሽፋን ሊኖረው ይገባል፤

(ሐ) የአንድ የህጻን አስከሬን ማረፊያ ጉድጓድ ርዝመቱ ከስር 1.5 ሜትር ከጉድጓዱ አፍ ላይ 1.6 ሜትር፣ ስፋቱ ከስር 0.6 ሜትርና ከጉድጓዱ አፍ ላይ 0.7 ሜትር፣ ጥልቀቱም 1.5 ሜትር መሆን አለበት፤

(መ) የህጻን አስከሬን ካረፈ በኋላ ከሳጥን በላይ ቢያንስ 0.9 ሜትር ሽፋን ሊኖረው ይገባል፤

(ሠ) በየአስከሬን ማሳረፊያ ጉድጓድ መካከል በ4ቱም አቅጣጫ የ0.6 ሜትር ርቀት መለያ ሊኖረው ይገባል፤

(ረ) የአስክሬኑ ማሳረፊያ ጉድጓድ በአራቱም ማዕዘን በባዞላ ድንጋይ መሸፈን ይኖርበታል፤ እንዲሁም አስክሬኑ ከስርም ከላይም በባዞላ መሸፈን አለበት፤

(ሰ) አስክሬኑን ከሸፈነው ባዞላ ድንጋይ ጀምሮ እስከ ጉድጓዱ አፍ ድረስ በአፈር መልሶ መሞላት አለበት፤

(ሸ) የቀብር ጉድጓድ አስከሬን ካረፈ በኋላ በአፈር በአግባቡ መደልደል አለበት፤

## 9. በዘላቂ ማረፊያ ጉድጓድ ላይ የሚተከል የራስጌ ምልክት ግንባታ ስታንዳርድ

(ሀ) የራስጌ ምልክት የሚቀመጥበት መሰረት ተቀባሪውን 20 ሴ.ሜ ጨምሮ ቁመቱ 40 ሴ.ሜ፣ ስፋቱ 70 ሴ.ሜ እንዲሁም ወረዱ 20 ሴ.ሜ መሆን አለበት፤

(ለ) የራስጌ ምልክት ሲሰራ ከመሬት በላይ በ70 ሴ.ሜ መሆን ያለበት ሲሆን ምልክቱ ብቻውን 50 ሴ.ሜ ቁመት፣ 40 ሴ.ሜ ስፋትና 10 ሴ.ሜ ውፍረት ያለው መሆን ይገባዋል፤

(ሐ) የሀውልቱ ጽሁፍ ይዘትም የሟቹን ስም፣ የውልደትና የዕረፍት ቀን/ወር/ዓ.ም በመሰረታዊነት የሚያካትት ሆኖ እንደየእምነቱና ፍላጎቱ ተጨማሪ አጫጭር ጽሁፎችንና ምልክቶችን ሊይዝ ይችላል፤ ጽሁፎቹና ምልክቶቹ የሙታንን ክብር የሚነኩና አጸያፊ መሆን የለባቸውም፤

(መ) የራስጌ ምልክቱ ከኮንክሪት አርማታ ወይም ከጥርብ ድንጋይ ወይም ከእምነበረድ የሚሰራ ሆኖ የሚቀባው ቀለም ነጭ መሆን አለበት፤ በምልክቱ ላይ የሚጻፉ ጽሁፎችና ምልክቶች ቀለም ጥቁር ሊሆን ይገባል፤

(ሠ) ለባይታዋር ቀብር መሰረቱን/ተቀባሪውን 20 ሴ.ሜ ጨምሮ 40 ሴ.ሜ ቁመት፣ 40 ሳ.ሜ ስፋትና ወርዱ 20 ሴ.ሜ የሆነ ከኮንክሪት የተሰራ ምልክት መቀመጥ አለበት፤ ምልክቱ ላይም የቀብሩ መለያ ኮድ ብቻ ሊሰፍርበት ይገባል፤

(ረ) ለስብስብ ቀብር የራስጌ ምልክት የሚቀመጥበት መሰረት እና የራስጌ ምልክት ሲዘጋጅ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ "ሀ" እና "ለ" የተቀመጡ ስታንዳርዶች ለዚህም ተፈጻሚ

ይሆናሉ፤ የራስጌ ምልክቱ ላይም የሞቱበትን ምክንያት፣ ቀንና ቦታ ገላጭ የሆነ ጽሁፍ መስፈር ይኖርበታል፤

(ሰ) በባይተዋር ቀብር ላይ የመታሰቢያ ራስጌ ምልክት አይተከልም፤ ነገር ግን የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ በባይተዋር ቀብር ላይ መለያ ምልክት ሊያስቀምጥ ይገባል፤

(ሸ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር በልዩ ምክንያቶች ፍቃድ ካልሰጠ በስተቀር በዚህ ስታንዳርድ መሰረት የተተከሉ የመቃብር ላይ ምልክቶችን ቅርጽና ይዘት መቀየር አይቻልም፤

(ቀ) አስቀባሪው ወይም አስቀባሪው የሚወክለው አካል በመቃብሩ ላይ የራስጌ ምልክት ማስቀመጥ ይችላል፤

(በ) የራስጌ ምልክት የሚቀመጥበት መሰረት /berm/ ርዝመቱ ቢበዛ 60 ሳ.ሜ፣ ወርዱ 30 ሳ.ሜ እና ውፍረቱ 20 ሳ.ሜ ሲሆን የራስጌ ምልክቱም በ20 ሳ.ሜ ጥልቀት መሰረቱ ላይ ሊተከል ይገባል፤

(ተ) የራስጌ ምልክት የሚቀመጥበት መሰረት /berm/ ከምድር በታች ቢያንስ 20 ሳ.ሜ ሊቀበር ይገባል፤

(ቸ) የራስጌ ምልክት የሚቀመጥበት መሰረት /berm/ በማለስለሻ /metal float/ በአግባቡ መለሰን አለበት፣

(ኀ) የራስጌ ምልክት የሚሰሩ አካላት ምልክቱን ካቆሙ በኋላ ስራውን በጨረሱ በ1 ቀን ውስጥ አካባቢውን ንጹህ አድርገው ለዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ማስረከብ አለባቸው፤

(ነ) የራስጌ ምልክት የሚገነቡ አካላት አጎራባች መቃብሮችን በማይጎዳና በማያበላሽ መልኩ ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፤

(ኘ) የራስጌ ምልክት የሚገነቡ አካላት፣ የጽዳትና ውበት ስራ የሚሰሩ እና ሌሎችም በቀብር ወቅት የቀብር ስነስርዓት ማወክ የለባቸውም፤

(አ) የራስጌ ምልክት ደህንነት የማስጠበቅ ሃላፊነት የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ይሆናል፤

(ከ) የራስጌ ምልክቱ ከመተከሉ በፊት የዝግጅት ስራው ከዘላቂ ማረፊያው ውጭ ተጠናቆ መቅረብ አለበት፤

(ኸ) በራስጌ ምልክት ላይ ቀድሞ ከተጻፈው ጽሁፍ ወይም ምልክት ሌላ በማናቸውም ሁኔታ ማሻሻል መፈቀድ የለበትም፤

(ወ) የራስጌ ምልክቱ በጉዳት ምክንያት ቢበላሽ እና መለወጥ ቢያስፈልግ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ በተመሳሳይ ጽሁፍና ምልክት ይዞ በሚዘጋጅ የራስጌ ምልክት ይተካዋል፤

(ዐ) የራስጌ ምልክቱ በሚጻዳበት ጊዜ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሆን ይገባዋል፤ የራስጌ ምልክቱን ገጽታ ሊያበላሹ በሚችሉ ኬሚካሎችና ቁሳቁሶች መታጠብ የለበትም፤

## 10. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ/ዴፖ /Depot for skeletons/

(ሀ) በዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ለአጽም የክብር ማሳረፊያ ቦታ/ዴፖ ሊዘጋጅ ይገባል፤ የዴፖውም መጠን ጥልቀቱ ከ5 ሜትር ያልበለጠ ሆኖ፣ ስፋቱ እና ርዝመቱ ቢያንስ 10ሜ በ5 ሜ መሆን አለበት፤

(ለ) ጉድጓዱ ውሃ አስርጎ እንዳያስገባና እንዳያስወጣ መገንባትና በአርማታ መለሰን ይኖርበታል፤

(ሐ) ወደ ጉድጓዱ መውረጃና መውጫ ደረጃ ሊሰራለት ይገባል፤

(መ) አጽም የሚቀመጥበት እና መለያ ኮድ የተዘጋጀለት መደርደሪያ መኖር አለበት፤

(ሠ) አጽም ወደ ክብር ማሳረፊያው ዴፖ በሚዛወርበት ጊዜ መለያ ኮድ ተሰጥቶትና ተመዝግቦ መግባት አለበት፤

(ረ) የአጽም የክብር ማሳረፊያ ዴፖው አጽም በሚዘዋወርበት ጊዜ እንዳይጨልምና እንዳያፍን መብራት እና የአየር ማናፈሻ /ventilator/ ሊገጠምለት ይገባል፤

(ሰ) ወደ አጽም የክብር ማሳረፊያ ዴፖው ጎርፍ እንዳያስገባ ዴፖው መግቢያ ከመሬት ቢያንስ 50 ሴንቲሜትር ከፍ ብሎ መሰራት እና በሚገባ መዘጋት አለበት፤

(ሸ) እንደ አስፈላጊነቱ ብዙ ሰው በአንድ ጊዜ የሚቀበርበት ስፍራ ሊዘጋጅ ይችላል፤

## 11. በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ የስብስብ አስከሬን ጉድጓድ አዘገጃጀት ስታንዳርድ

### 11.1. የስብስብ አስከሬን ቀብር የሚፈቀደው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል፤

(ሀ) በድንገተኛ አደጋ ወይም በሌላ ምክንያቶች ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ በሚሞቱበትና ለእያንዳንዳቸው የመቃብር ጉድጓድ ለመቆፈር አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ፤

(ለ) የአንድ ቤተሰብ አባላት በአንድ ጊዜ ሲሞቱ እና አስቀባሪው በአንድ ጉድጓድ እንዲቀበሩለት ጥያቄ ካቀረበ፤

### 11.2. የስብስብ አስከሬን ጉድጓድ አዘገጃጀት ስታንዳርድ

(ሀ) አንድ የስብስብ ቀብር ከ10 አስከሬን በላይ መያዝ የለበትም፤

(ለ) የአንድ ስብስብ አስከሬን ቀብር ጉድጓድ ርዝመቱ ከስር 2.4 ሜትር ከጉድጓዱ አፍ ላይ 2.5 ሜትር፣ ጥልቀቱም 2 ሜትር መሆን ያለበት ሲሆን ስፋቱ ግን እንደ የሚቀበረው አስከሬን ብዛት በ0.9 ሜትር ተባዝቶ የሚዘጋጅ ይሆናል፤

(ሐ) በስብስብ ዘላቂ ማረፊያ ጉድጓድ ውስጥ የተቀበሩ አስከሬኖች ቆፍሮ የማውጣት ፈቃድ መስጠት የለበትም፤ ይሁንና የአንድ ቤተሰብ አባላት በጉድጓዱ ውስጥ ከተቀበሩ መረጃዎችን በማጣራት የአስከሬን ቆፍሮ ማውጣትና ማዘዋወር ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

# ክፍል አራት፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ የአስተዳደር ስታንዳርድ

## 12. የምድረ-ግቢው የአስተዳደር ስታንዳርድ

### 12.1. አጠቃላይ መሥፈርት

(ሀ) ማንኛውም ከተማ በማዘጋጃ ቤቱ ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት የሚተዳደር የማዘጋጃ ቤታዊ የዘላቂ ማረፊያ ሊኖረው ይገባል፤

(ለ) ከተማው የሚያዘጋጀው የዘላቂ ማረፊያ ሁሉንም ሃይማኖቶች እና የባይተዋር ቀብርን ለየብቻቸው ሊያስተናግድ የሚችል መሆን አለበት፤

(ሐ) ከዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ፍቃድ ሳይሰጠው ማንኛውም አካል በዘላቂ ማረፊያ ቅጽር ግቢ ውስጥ ቀብር ሊፈጽም አይችልም፤

(መ) ለአንድ አስከሬን ቀብር የሚዘጋጀው የቀብር ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ ነው፤ በማናቸውም ሁኔታ የቀብር ስፍራ ሰው ሳይሞት አስቀድሞ ማዘጋጀት ወይም መያዝ መፈቀድ የለበትም፤

(ሠ) በዘላቂ ማረፊያ የቀብር ስነስርዓት የሚፈጸመው እንደ አመጣጡ ቅደም ተከተል በመደዳ በሚዘጋጁ መቃብሮች ይሆናል፤ በአስቀባሪ ወዳጅ ዘመዶች ምርጫ የመቃብር ጉድጓድ በዘፈቀደ አይቆፈርም፤

(ሰ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ በአገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ በተጠቃሚዎች ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ መስጠት ይኖርበታል፤

### 12.2. የቀብር ፍቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ አቀራረብ

(ሀ) የቀብር ፍቃድ አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዩ በዕዝል 1 አባሪ የተደረገውን የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቀብር አገልግሎትና የራስጌ ምልክት መትከያ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001 ሞልቶ ለዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

(ለ) የቀብር አገልግሎት ለማግኘት ማመልከቻ ያቀረበ አስቀባሪ በተለያዩ ምክንያቶች በተያዘለት የጊዜ ገደብ ቀብሩን ማከናወን ባለመቻሉ ወደ ሌላ ቀን እንዲተላለፍለት ቢያንስ የቀብሩ ሰዓት ከመድረሱ ከ4 ሰዓት በፊት ለዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ ማሳወቅ አለበት፤

## 12.3. መረጃ አያያዝና አስተዳደር

(ሀ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ የእያንዳንዱን ቀብር መረጃዎች መመዝገብና መያዝ ያለበት ሲሆን ለቅርብ ተጠሪውም መረጃው በኮፒ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፤

(ለ) መረጃውም የሚመዘገበው የቀብር ስነስርዓቱ በተፈጸመ በ1 ቀን ውስጥ ነው፤

(ሐ) ተመዝግቦ የተያዘው መረጃ በእሳት አደጋና በሌሎች ምክንያቶች ጉዳት በማይደርስበት ሁኔታ ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲቀመጥ በሚያስችል አያያዝ መቆየት አለበት፤

(መ) በዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ የተመዘገቡ የቀብር መረጃዎችን ማየት የሚፈልግ አካል የጽሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ በስራ ሰዓት ሊመለከታቸው ይችላል፤

(ሠ) ከቀብር ማስፈጸም ጋር የተያያዙ የንግድ ተቋማት የዘላቂ ማረፊያውን የተመዘገቡ መረጃዎች ለንግድ ስራ እንዲጠቀሙበት መፈቀድ የለበትም፤

(ረ) የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ወደ ዘላቂ ማረፊያው ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለትምህርት ለሚመጡ አካላት ተፈላጊውን መረጃ መስጠትና ማሳየት አለበት፤

# 13. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቀብር ስርዓት አመዘጋገብ /Burial registers/

በዘላቂ ማረፊያው የቀብር ስርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ዝርዝር መረጃ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፤ የሚመዘገበውም መረጃ የሚከተለውን ዝርዝር ማካተት ይኖርበታል፡-

(ሀ) የሟች ሙሉ ስም ከነአያት፣

(ለ) የነዋሪነት መታወቂያ ቁጥር እና ጾታ፣

(ሐ) የውልደት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም፣

(መ) የሞተበት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም፣

(ሠ) የሞተበት ምክንያት፣

(ረ) የሞተበት ቦታ፣

(ሰ) የባይተዋር ቀብር አገልግሎት ከሆነ ከፖሊስ ወይም ከጤና ተቋማት የተጻፈ የደብዳቤ ቁጥርና ቀን፣

(ሸ) በየትኛው የቀብር ክፍል /መደበኛ ወይም ባይታወር/ የቀብር ስነ-ስርዓቱ እንደተከናወነ፤

(ቀ) የመቃብር ሽንሻኖ መለያ ኮድ፤

(በ) ቀብር የተፈጸመበት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም፤

(ተ) በአጽም ዝውውር ወቅት አጽሙ ተቆፍሮ የወጣበት ዘላቂ ማረፊያ ስም፤

(ቸ) መረጃው የተሞላበት ቀን፣ ወር ዓ.ም፣

(ነ) መረጃውን ያስሞላው የሟች ዘመድ ስም፤

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- በስታንዳርዱ ከተቀመጠው አስከሬን ማሳረፊያ ጉድጓድ መጠን ከፍ ያለ ጉድጓድ በሚያስፈልግበት ጊዜ ጉድጓዱ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ ሲሰጥ የጉድጓዱ መጠን ከፍ ያለ መሆን እንዳለበት የአስክሬኑ መጠን ተገልጾ መጠየቅ አለበት፤

## 14. የአስከሬን ሳጥን ስታንዳርድ

(ሀ) የአስከሬን ሳጥን ከእንጨት ወይም በቀላሉ ሊበሰብስ በሚችል ቁስ ሊሰራ ይገባል፤

(ለ) በአንድ የአስከሬን ሳጥን ውስጥ ከአንድ አስከሬን በላይ ከትቶ መቅበር መፈቀድ የለበትም፤

(ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ጊዜው ደርሶ አጽሙ እንዲወጣ የተደረገ መቃብር ለሌላ ቀብር አገልግሎት እንዲውል በአዲስ መልክ መዘጋጀት አለበት፤

## 15. የቀብርና ሌሎች ተዛማጅ የዘላቂ ማረፊያ አገልግሎቶች መስጫ የስራ ሰዓት

(ሀ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ቀብር የሚፈጸመው ዘወትር ከጥዋቱ 2፡30 እስከ 11፡00 ድረስ መሆን አለበት፤

(ለ) የቀብር ጉድጓድ ዝግጅት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ መሆን አለበት፤

(ሐ) በተለዩ ሁኔታዎች አስገዳጅነት በስታንዳርዱ ከተቀመጠው ሰዓት ውጭ የቀብር ስርዓት ማከናወን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ምክንያቱን በመግለጽና ማመልከቻ በማቅረብ ሊፈቀድ ይችላል፤

(መ) የዘላቂ ማረፊያዎች ዘወትር ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 11፡30 ለጎብኚዎች ክፍት መሆን አለባቸው፤ ሆኖም ግን አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በውል ለታወቀ የተወሰነ ጊዜ ዘላቂ ማረፊያውን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለጎብኚዎች ዝግ ሊያደርግ ይችላል፤

ይህንንም በዘላቂ ማረፊያው መግቢያ አካባቢ በሚገኘው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለህዝብ ማሳወቅ አለበት፤

## 16. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ በቀብር ስነ-ስርዓት ላይ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና የመታሰቢያ ሥነ-ሥርዓት

(ሀ) በዘላቂ ማረፊያ ውስጥ በቀብር ወቅትም ይሁን ከቀብር ውጭ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና የመታሰቢያ፣ ስርዓት መከወን የሚቻል ሲሆን ይህም የሚፈጸመው በዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር እውቅናና ቁጥጥር ስር ይሆናል፤

(ለ) በዘላቂ ማረፊያ ውስጥ በቀብር ወቅትም ይሁን ከቀብር ውጭ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና የመታሰቢያ ስርዓት መከናወን የሚችለው ቀብሩ በተፈጸመበት የመቃብር ክልል ውስጥ ብቻ ነው፤

(ሐ) በቀብር ስነስርዓት ላይ ለቀብር አስፈጻሚዎች ተፈላጊውን ወጭ ሁሉ (ጉድጓድ ማስቆፈር፣ የአስከሬን ሳጥን ማጓጓዝ፣ መቅበርና አፈር ማልበስ) ማሟላት ያለበት አስቀባሪው ነው፤

(መ) በቀብር ወይም ከቀብር ውጭ የሚከናወኑ ሃይማታዊ፣ ባህላዊ እና የመታሰቢያ ስርዓቶች ሊከናወኑ የሚችሉበትን የሰዓት ገደብ የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ሊወስን ይችላል፤

## 17. ቀብር አስፈጻሚዎች

(ሀ) ቀብር አስፈጻሚዎች ከዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር የሙያና የስራ ፈቃድ ሊያወጡ ይገባል፤

(ለ) የቀብር አስፈጻሚዎችን የስራ ብቃት የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር እየተከታተለ መመዘን ይኖርበታል፤

(ሐ) ቀብር አስፈጻሚዎች በዚህ ስታንዳርድ በተቀመጠው መሰረት ስራቸው ማከናወን አለባቸው፤

(መ) በቀብር ስነስርዓት ወቅት የቀብር አስፈጻሚው ለቀብር የተጠቀመበትን መሳሪያ እንዲሁም የተራረፈ አፈር በማንሳት አካባቢውን ንጹህ ማድረግ አለበት፤

## 18. የአስከሬን ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ስታንዳርድ

(ሀ) የሜትሮፖሊስ እና የሪጂዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች ማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ለአስከሬን ማጓጓዣ ተብሎ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ /hearses/ ሊኖራቸው ይገባል፤ ነገር ግን በፈርጅ አንድና ቀጥሎ ባሉት ከተሞች ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡

(ለ) የዘላቂ ማረፊያ የአስከሬን ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ለባይተዋር አስከሬን የነጻ አገልግሎት መስጠት የሚገባው ሲሆን ዘመድ ወዳጅ ላለው አስከሬን ግን በኪራይ ሊያቀርብ ይችላል፤

## 19. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ መድረ ግቢ ውስጥ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ስታንዳርድ

(ሀ) በዘላቂ ማረፊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማንኛውም የተሽከርካሪ እንቅስቃሴን የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር መቆጣጠር ይኖርበታል፤

(ለ) ማንኛውም ተሽከርካሪ በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ለተሽከርካሪ ከተፈቀደው መንገድና ማቆሚያ ውጭ መንቀሳቀስም ሆነ ማቆም አይፈቀድለትም፤

(ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ከ20 ኪ.ሜ በላይ በሰዓት ማሽከርከር መፈቀድ የለበትም፤ ይህም በተገቢው የትራፊክ ምልክት መገለጽ አለበት፤

## 20. የአስከሬን የማጓጓዝ ስታንዳርድ

(ሀ) አስከሬን ሲጓጓዝ በጥንቃቄና ምቹ በሆነ ሁኔታ ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ሆኖ መሆን አለበት፤

(ለ) በማናቸውም ሁኔታ የአስከሬኑን ክብር ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ አስከሬኑን ማጓጓዝ አይፈቀድም፤

(ሐ) አስከሬን ሲጓጓዝ በማናቸውም ሁኔታ የአስከሬኑን ክብር በሚያዋርድ መልክ ማንኛውም የአካሉ ክፍል መጋለጥ የለበትም፤

(መ) በተለየ ባህል ወይም ሃይማኖት ስርዓት ምክንያት ከላይ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች ማሟላት ባይቻል በቅድሚያ ከዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ፍቃድ ሊሰጠው ይገባል፤

(ሠ) አስቀባሪው አስከሬኑን ወደ መቅበሪያ ቦታ የማጓጓዝ ሃላፊነት አለበት፤

## 21. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የጽዳትና ውበት ስታንዳርድ

### 21.1. የጽዳት አጠባበቅ ስታንዳርድ

(ሀ) በማንኛውም ጊዜ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ጽዱ መሆን ይገባዋል፤

(ለ) በዘላቂ ማረፊያ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ የቀብር ቦታዎችንና የሀዘንተኞች መሰብሰቢያ ቦታዎችን /አደባባዮችን/ ማጽዳት፣ መንገድና መንገድ ዳርቻዎችን፣ የውሀ መውረጃ ቦዮችንና አረንጓዴ ቦታዎችን መጥረግ፣ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች (ደስት ቢኖች) ውስጥ ቆሻሻን ማሰባሰብን ያጠቃልላል፡፡

(ሐ) በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብ እና አወጋገድ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጸድቆ በወጣው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስታንዳርድ ቁጥር ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር 07፡2007 መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፤

(መ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ በመንገዶች ዳርቻ፣ በአደባባይ ዳርቻ፣ ሀዘንተኞች በሚሰባሰቡበት ቦታ ላይ ለጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያ የሚያገለግል ደስት ቢን መቀመጥ ያለበት ሲሆን ዲዛይኑና አቀማመጡም ከላይ በፊደል "ሐ" በተጠቀሰው ስታንዳርድ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆን አለበት፤

(ሠ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ከሚገኘው ከአስተዳደር ህንጻውና ከህዝብ መጸዳጃ ቤት የሚመነጭ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጸድቆ በወጣው የህዝብና የጋራ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ የህንጻው የውስጥ ዲዛይን፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የስራ አመራር ስታንዳርድ ቁጥር ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር 28፡2007 መሠረት መሆን አለበት፤

(ረ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር በሥሩ ላሰማራቸው ሰራተኞች በዚህ ስታንዳርድ አንቀጽ 26.4 በተቀመጠው መሰረት የደህንነትና የንጽህና መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያዎች በወቅቱ ማቅረብ፣ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች በስራ ወቅት የግል ደህንነት መከላከያ አልባሳትንና ቁሳቁሶችን በተገቢው ሁኔታ ስለመጠቀማቸው መከታተል እና ለዘላቂ ማረፊያው አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን ማቅረብ አለበት፤

## 21.2. ለጽዳትና ውበት ስራዎች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ለጽዳትና ውበት ስራዎች ቢያንስ የሚከተሉት መሳሪያዎች መሟላት አለባቸው፡-

የቁም መጥረጊያ፣ መወልወያ፣ መወልወያ ብሩሽ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት/waste bin/ እና ገንዳ፣ የእጅ ጋሪ፣ ባሬላ፣ መቧጠጫ /ሬክ/፣ ማጭድ፣ ገጀራ፣ ዶማ፣ አካፋ፣ የውሀ ማጠጫ የላስቲክ ቱቦ፤

### 21.3. የዘላቂ ማረፊያ እንክብካቤና በአትክልት የማስዋብ ስራ

(ሀ) ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ የዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢውን የማስዋብና የመንከባከብ ሃላፊነት አለበት፤

(ለ) የመቃብር ደህንነት የመጠበቅ ስራ የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ሃላፊነት ነው፤

(ሐ) ቀብር ከተፈጸመበት ቀን ውጭ ማንኛውም ሰው በመቃብሩ ላይ ማስጌጫ ቁሳቁስን መትከል፣ ማስቀመጥና ትቶ መሄድ የለበትም፤ ነገር ግን ከሃውልቱ ጋራ አብሮ በተሰራው የአበባ ማስቀመጫ ላይ የተፈጥሮ አበባ ብቻ ማስቀመጥ ይቻላል፤

(መ) በመቃብር ላይ ዛፍና ቁጥቋጦዎችን መትከል በማናቸውም ሁኔታ መፈቀድ የለበትም፤

(ሠ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ መቃብር ላይ የተቀመጡ የተፈጥሮ አበባዎች ሲጠወልጉ ወይም ሲጎዱ ማስወገድ ይኖርበታል፤

(ረ) የዘላቂ ማረፊያው ሰራተኞች በማንኛውም የዘላቂ ማረፊያ የቀብር ክልል በሚደለድሉበትና በሳር በሚያስውቡበት ወቅት ማንኛውም አካል ስራቸውን ማስተጓጎል የለበትም፤

(ሰ) ዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ከቀብር በኋላ በመቃብሩ ዙሪያ የተዝረከረከ አፈርና ቆሻሻን በእለቱ ማጽዳትና ማንሳት አለበት፤

(ሸ) ከዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ፍቃድ ውጪ ምንም ዓይነት አፈር ከመቃብሩ ላይ መነሳትና መወገድ የለበትም፤

(ቀ) አስቀባሪው ከዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር በሚሰጠው ፍቃድና መመሪያ መሰረት መቃብሩን የመጠገንና የመንከባከብ ስራ ሊያከናውን ይችላል፤ ይሁን እንጂ አስተዳደሩ በራሱ ወጪ መቃብሩን የመጠገን እና የመንከባከብ ስልጣኑ የተጠበቀ ነው፤

## 22. የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የአገልግሎት መጠቀሚያ ታሪፍ

(ሀ) የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያዎች ለሚሰጡት አገልግሎቶች ከተማ አስተዳደሩ ታሪፍ መወሰንና እንዳስፈላጊነቱ መከለስ ያለበት ሲሆን የታሪፍ አወሳሰኑ የተጠቃሚውን የኢኮኖሚ አቅም ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፤

(ለ) ማንኛውም ተገልጋይ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ለማግኘት ከተማ አስተዳደሩ በሚወስነው ታሪፍ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፤

(ሐ) የሚተመነው የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ተገልጋዩ በግልጽ ሊያየው በሚችል ቦታ መለጠፍ አለበት፤

(መ) ተገልጋይ ለሚከፍለው ክፍያ ደረሰኝ ሊሰጠው ይገባል፤

## 23. የሰራተኞች የግል ደህንነትና ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች /personal protective equipment/

23.1. በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር የቀብር ስራ ለሚሰሩ ሰራተኞች /የቀብር ጉድጓድ ቆፋሪዎች፣ ቀባሪዎች፣ የራስጌ ምልክት አዘጋጆችና ተካዮች/ እና የጽዳትና ውበት ስራ ለሚሰሩ ሰራተኞች፣ ለጥበቃዎች ቢያንስ የሚከተሉት የግል ደህንነት መከላከያ አልባሳትና ቁሳቁሶች ሊሟላላቸው ይገባል፡፡

(ሀ) ቆዳ ወይም ቦት ጫማ፣ የደንብ ልብስ፣ ቱታ፣ ጠንካራ ጓንቶች፣ የአፍ፣ የአፍንጫና የጭንቅላት መሸፈኛ /ማስክ/፣ አንጸባራቂ ሰደርያ፤

(ለ) የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን /first aid kit/ ፤

(ሐ) ለሰራተኞች የንጽህና መጠበቂያ ሳሙና፣ ኦሞ፣ ሶፍት የመሳሰሉት ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፤

### 23.2. የሰራተኞች ጤና እና ደህንነት

(ሀ) ለሰራተኞች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ /በየስድስት ወሩ/ የጤና ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል፤

(ለ) የአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች የጤና ኢንሹራንስ ሊኖራቸው ይገባል፤

(ሐ) የሰራተኞች ጤንነትን ለመጠበቅ እንዲረዳ በየቀኑ ቢያንስ አንድ ሊትር ወተት ሊቀርብላቸው ይገባል፤

(መ) የሚመለከታቸው የዘላቂ ማረፊያው የስራ ኃላፊዎች ሁሉም የሚከሰቱ አደጋዎችና ክስተቶች የሚመዘገቡበትና የሚያጣሩበት የሪፖርት ስርዓት እንዲሁም አደጋ ሲደርስ አደጋ የደረሰባቸውን የሚታደጉበት ስርዓት መዘርጋት አለባቸው፤

(ሠ) በዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ሥር ለሚሰሩ ሰራተኞች በስራ ወቅት ሊያጋጥሟቸዉ የሚችሉ የአደጋ መንስኤዎችና የመከላከያ ዘዴዎችን እንዲገነዘቡ ለማድረግ የጤና አጠባበቅ እና የደህንነት ስልጠናዎችን መስጠት ያስፈልጋል፤

(ረ) ሁሉም ሰራተኞች የሚሰጣቸውን የደንብና የደህንነት መጠበቂያ አልባሳት በተገቢው ቦታና ጊዜ መልበስ አለባቸው፤

(ሰ) የግል ጤንነትና ደህንነት መጠበቅያ መሳሪያዎች በየስድስት ወሩ ወይም ቀድመው ከጥቅም ውጭ ከሆኑ ከስድስት ወር በፊት በሚመለከተው የስራ ክፍል ወይም ኮንትራት ወስዶ አገልግሎት በሚያቀርበው አካል መቀየር አለባቸው፤

(ሸ) የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ለግል ጤናና ንጽህና መጠበቂያነት የሚያገለግሉ ሳሙና፣ ኦሞ፣ መጥፎ ሽታንና ተህዋስያንን የሚያስወግዱ እንዲሁም መልካም መዓዛ የሚፈጥሩ የጽዳት ኬሚካሎች /detergents & disinfectants/ ሊያሟላ ይገባል፤

(ቀ) የተሟላ የግል ጤናና ደህንነት መጠበቅያ መሣሪያ ለሁሉም ሰራተኞች መሟላታቸውን እና መሳሪያዎቹን ዘወትር በስራ ወቅት መጠቀም አስፈላጊ የስራ ላይ ግዴታ መሆን አለበት፤

## 24. ስልጠና

(ሀ) ሁሉም በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ስራ ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሰራተኞች ቢያንስ አግባብነት ያለው የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፤

(ለ) የሚመለከተው አካል በዘርፉ የተሰማሩ ሠራተኞች አዲስ የሚቀጠሩ ሰራተኞችንም ጨምሮ ስልጠና መውሰዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

(ሐ) በስልጠና ፕሮግራም ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች ምን እንደሚያስታውሱና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የመመዘኛ ፈተና መውሰድ አለባቸው፤ ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉ ከሆኑ ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ የሚጠይቅ በቪዲዮ ወይም በፎቶግራፍ የተደገፈ የመመዘኛ ፈተና ሊቀርብላቸው ይገባል፤

(መ) የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ በስሩ ላሉ ሰራተኞች የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ አሰጣጥን ጨምሮ አግባብነት ያለው ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት አለበት፤

## 25. የስራ ላይ ደህንነት

(ሀ) ሁሉም ሰራተኞች በደህንነት ጉዳዮች የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው፤ እንዲሁም ስልጠናው ተገቢ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፤

(ለ) ስልጠናው በዘላቂ ማረፊያው የሚሰሩ ሰራተኞች የሚያጋጥማቸውን የተለያዩ አደጋዎች በመከላከል ላይ ያተኮረ መሆን አለበት፤

## 26. የህዝብ ግንኙነት ስራዎች

የዘርፉን አገልግሎትና ጠቀሜታ የከተማው ነዋሪ ህዝብ በውል እንዲገነዘበውና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ መጠቀም እንዲችል፤ እንዲሁም ሌሎች የመሚመለከታቸው አካላት እንዲጠቀሙበት የተለያዩ መንገዶችን /ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ የማስተዋወቅና መልዕክት የማስተላለፍ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሠራ ይገባል፡፡

ይህ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጸደቀበት ከመጋቢት 06 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ በከተሞች ተግባራዊ ይሆናል፡፡

______________

አምባቸው መኮንን (ዶ/ር)

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

# ዕዝሎች

## ዕዝል አንድ፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ ውስጥ ከከተሞች ፈርጅ አንፃር ያሉትን ልዩነቶች ማሳያ/መጠቆሚያ ሠንጠረዥ፤

ይህ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት ስታንዳርድ በሁሉም የአገሪቱ ከተሞች የሚተገበር ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ የተመለከቱት ነጥቦች ብቻ ከከተሞች ፈርጅ አንፃር ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

| አንቀጽ | በሜትሮፖሊስ አስተዳደር የሚተገበር | በሪጅዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች የሚተገበር | በፈርጅ አንድ እና ቀጥሎ ባሉት ከተማ አስተዳደሮች የሚተገበር |
|---|---|---|---|
| 6.2.1.1 | ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ዋና መግቢያ በር ላይ፣ ጥበቃ ማማ ባለበት አካባቢ፣ በመንገዶች ዳርቻ እና በመቃብር ስፍራዎች መብራት መገጠም አለበት፤ | ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ዋና መግቢያ በር ላይ፣ ጥበቃ ማማ ባለበት አካባቢ፣ በመንገዶች ዳርቻ እና በመቃብር ስፍራዎች መብራት መገጠም አለበት፤ | ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ዋና መግቢያ በር ላይ፣ ጥበቃ ማማ ባለበት አካባቢ፣ በመንገዶች ዳርቻ እና በመቃብር ስፍራዎች እንዳስፈላጊነቱ መብራት መገጠም አለበት፤ |
| 6.2.1.2 | ሐ/ ጽሁፉ በምሽት በግልጽ እንዲነበብ መብራት ሊገጠምለት ይገባል፤ | ሐ/ ጽሁፉ በምሽት በግልጽ እንዲነበብ መብራት ቢገጠምለት ይመረጣል፤ | አልተካተተም |
| 6.2.7 | ሐ/ ከአስከሬኑ ማሳረፊያ ፊትለፊት የሀዘንተኞች እና የቀባሪዎች ማሳረጊያና ማረፊያ ቦታ የሚኖረው ሲሆን ይህም ቦታ ለፀሐይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ እና ለማረፊያ የሚሆን መቀመጫ ሊዘጋጅለት ይገባል፤ | ሐ/ ከአስከሬኑ ማሳረፊያ ፊትለፊት የሀዘንተኞች እና የቀባሪዎች ማሳረጊያና ማረፊያ ቦታ የሚኖረው ሲሆን ይህም ቦታ ለፀሐይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ እና ለማረፊያ የሚሆን መቀመጫ ሊዘጋጅለት ይገባል፤ | ሐ/ ከአስከሬኑ ማሳረፊያ ፊትለፊት የሀዘንተኞች እና የቀባሪዎች ማሳረጊያና ማረፊያ ቦታ የሚኖረው ሲሆን ይህም ቦታ ለፀሐይና ለዝናብ መከላከያነት የሚያገለግል መጠለያ እና ለማረፊያ የሚሆን መቀመጫ ቢዘጋጅ ይመረጣል፡፡ |
| 6.2.9 | ii- ሀ) መቀመጫዎቹም ከኮንክሪት ወይም ከብረት ሊሰሩ ይገባል፤ | ii- ሀ) መቀመጫዎቹም ከኮንክሪት ወይም ከብረት ሊሰሩ ይገባል፤ | ii- ሀ) መቀመጫዎቹም ከኮንክሪት ወይም ከብረት ወይም ከእንጨት |

| አንቀጽ | በሜትሮፖሊስ አስተዳደር የሚተገበር | በሪጅዮፖሊስ አስተዳደር ከተሞች የሚተገበር | በፈርጅ አንድ እና ቀጥሎ ባሉት ከተማ አስተዳደሮች የሚተገበር |
|---|---|---|---|
| | | | ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| 18 | ሀ/ አንድ ዘላቂ ማረፊያ ለአስከሬን ማጓጓዣ ተብሎ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ /hearses/ ሊኖረው ይገባል፡፡ | ሀ/ አንድ ዘላቂ ማረፊያ ለአስከሬን ማጓጓዣ ተብሎ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ /hearses/ ሊኖረው ይገባል፡፡ | ሀ/ አንድ ዘላቂ ማረፊያ ለአስከሬን ማጓጓዣ ተብሎ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ /hearses/ ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡ |

**ዕዝል 2፡- የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ የቀብር አገልግሎትና የራስጌ ምልክት መትከያ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-001**

ቀን……………..……………..

ለ…………………..…………..

<u>የከተማው ስም</u>፣

1. የአመልካች ስም………………………………..
2. የጠየቁት የቀብር ዓይነት
   i. መደበኛ………………… የራስጌ ምልክት…………………
   ii. ባይተዋር………………..
   iii. ስብስብ…………………. የራስጌ ምልክት…………………
3. የሟች ሙሉ ስም ከነአያት…………………………
4. ጾታ…………………………
5. ሟች ይከተለው የነበረው እምነት…………………..
6. የነዋሪነት መታወቂያ ቁጥር……………………
7. የውልደት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም……………….
8. የሞተበት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም……………….
9. የሞተበት ምክንያት……………………..
10. የሞተበት ቦታ…………………………..

የአገልግሎት ጠያቂው ሥም…………………………

ፊርማ……………………

ማሳሰቢያ፡- 1/ ባይተዋር ቀብር አገልግሎት ከሆነ ከፖሊስ ወይም ከጤና ተቋማት የተጻፈ ደብዳቤ ከማመልከቻ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

2/ የራስጌ ምልክት ላይ የሚሰፍሩ አጫጭር ጽሁፎችና ምልክቶች ከማመልከቻ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ አለበት፤

## ዕዝል 3፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያው ምድረግቢ ውስጥ ስርዓተ ቀብር የተፈጸመ ስለመሆኑ ማስረጃ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-002

ቀን..........................

ለ.......................

<u>የከተማው ስም</u>

አመልካች እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት.........................ነዋሪነቴ በ...............................ከተማ፣ በ....................................ክ/ከተማ፣ በ......................ወረዳ/በ.....................ቀበሌ ሲሆን ሟች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት............................በ....................ቀን (ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም) ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በዚሁ ዘላቂ ማረፊያ ስርዓተ ቀብራቸው መፈጸሙ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሠረት የዘላቂ ማረፊያ ማስረጃ እንዲሰጠኝ በማለት አመለክታለሁ፡፡

የአገልግሎት ጠያቂው ሥም................................

ፊርማ...................................

## ዕዝል 4፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያው ምድረገቢ ውስጥ ስርዓተ ቀብር የተፈጸመ ስለመሆኑን ማስረጃ ቅጽ ዘማ-003

ቁጥር……………………

ቀን………………………

<u>ለሚመለከተው ሁሉ</u>

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት……………………..……የሟች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት…………………የቀብር ማስረጃ እንዲሰጣቸው በ…..…………………ቀን (ቀን፣ ወርና ዓ.ም.) በጽሑፍ ማመልከቻ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ሟች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት…………………….…….በ………………..ቀን (ቀን፣ ወርና ዓ.ም.) ሥርዓተ ቀብራቸው በዘላቂ ማረፊያችን በዚህ ዕለት የተፈጸመ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ማኅተም

## ዕዝል 5፡- ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-004

ቀን……………………..

ለ……………………..………..ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር ጽ/ቤት
<u>የከተማው ስም</u>

አመልካች እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት…………………..……ነዋሪነቴ በ……….………...………ከተማ በ…………………………..…………ክ/ከተማ………………………………..…ወረዳ/ቀበሌ ሲሆን ሟች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት…………………….……በዚሁ ዘላቂ ማረፊያ በ…………………..ቀን (ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም) የተቀበሩ በመሆኑ አስከሬናቸውን/አጽማቸውን ወደ …………………………………..ለመውሰድ ስለምፈልግ አጽሙን ለማዘዋወር እንዲፈቀድልኝ እያመለከትኩ ከሟች ጋር ያለኝን ዝምድና……………………………….መሆኑን ጭምር እገልጻለሁ፡፡

የአገልግሎት ጠያቂው ሥም……………………………..
ፊርማ……………………………..

<u>ማሳሰበቢያ</u>፡- የተጠቀሰውን ዝምድና የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ ከዚህ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

**ዕዝል 6፡- ከማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስከሬን/አጽም ወደ ሌላ አድራሻ የማዛወር ፈቃድ መስጫ ቅጽ ዘማ-005**

ቁጥር..............................

ቀን..................................

**ለ....................................**

**የከተማው ስም፣**

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት...........................................የሚች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት......................አስከሬን /አጽም/ የማዘዋወር ፈቃድ እንዲሰጣቸው በ............................ቀን (ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም) ባቀረቡት ማመልከቻ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ የጠየቁትን አስከሬን /አጽም/ እንዲያዘዋውሩ የተፈቀደላቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ማኅተም

## ዕዝል 7፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ለቁሳቁስ አቅርቦት ለማህበራትና ለግል ድርጅቶች ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ዘማ-006

ቀን……………………..

ለ……………………………..

<u>የከተማው ስም</u>

1. የአመልካች ስም………………………………..
2. አድራሻ…………………………………………
3. ከተማ…………….………………………....
4. ክ/ከተማ……………………………………..…
5. ወረዳ……………………………………….….
6. ቀበሌ……………………………………………
7. አመልካች የተሰማራበት የሙያ ዘርፍ……………………………….

በ………………………………………ማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ከሚሰሩ ስራዎች ውስጥ የሚከተሉትን ለማከናወን የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ ፈቃድ እንዲሰጠን እንጠይቃለን፤

ሀ/ የጉድጓድ ዝግጅት ስራ…………..…..

ለ/ ቀብር የመፈጸም ስራ………….…...

ሐ/ የራስጌ ምልክት ዝግጅትና ተከላ ስራ……………….

መ/ ለዚሁ ስራ ማስፈጸሚያነት የሚውሉ ቁሳቁስ አቅርቦት ለማከናወን………………

ሠ/ አጽም ከመቃብር ወደ ዴፖ የማዛወር ስራ…………………….

የአገልግሎት ጠያቂው ሥም……………………………..

ፊርማ……………………………..

## ዕዝል 8፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ለቁሳቁስ አቅርቦት ለማህበራትና ለግል ድርጅቶች ፈቃድ መጠየቂያ መስጫ ቅጽ ዘማ-007

ቁጥር......................

ቀን.........................

ለ..................................ከተማ አስተዳደር የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደር/ ጽ/ቤት
የከተማው ስም፣

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት...........................................በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ...................................................ስራን /ስራዎችን/ ለመስራት ፈቃድ እንዲሰጣቸው በ............................ቀን (ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም) ባቀረቡት ማመልከቻ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩ ጉዳዩን ከተመለከተና የቀረቡ ማስረጃዎችን ካጣራ በኋላ በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ቁሳቁስ እንዲያቀርቡ የፈቀደላቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ማኅተም

## ዕዝል 9፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረግቢ ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎችና ለቁሳቁስ አቅርቦት ለማህበራትና ለግል ድርጅቶች ፈቃድ የግዴታ ማስገቢያ ቅጽ ዘማ-008

1. የማህበሩ/ የድርጅቱ ስም………………
2. ፍቃድ የተሰጠበት ቀን (ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም)…………………….
3. የውል ሰጪው ሃላፊነትና ግዴታዎች…………
4. የውል ተቀባይ ሃላፊነትና ግዴታዎች…………..
5. የውል ዘመን…………………….

የውል ሰጪው ስም………………….. ፊርማ………….………

የውል ተቀባይ ስም……………..… ፊርማ………………………..

ማኅተም

## ዕዝል 10፡- በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ሥርዓተ ቀብር ስለመፈጸሙ የሚሰጥ ማስረጃ የምስክር ወረቀት ይዘት

በማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ ምድረ ግቢ ውስጥ ሥርዓተ ቀብር ስለመፈጸሙ የሚሰጥ ማስረጃ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ/ የሟችን ሙሉ ስም፣ ማእረግ፣ ጾታ፣ እድሜ፣ ሥራ፣ መደበኛ መኖሪያ፣ ዜግነትና ሃይማኖት፤

ለ/ የተቀበረበት ቀን፣ ምክንያትና ካለም ሞቱን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ የሚያመለክት መግለጫ፤

ሐ/ የዘላቂ ማረፊያው አስተዳደር ሃላፊ እና ማስረጃውን ያዘጋጀው ፈጻሚ ስምና ፊርማ፣ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ማህተም፤

መ/ የዘላቂ ማረፊያ አስተዳደሩን ስልክ ቁጥር፣ ፋክስ ቁጥር፣ ፖስታሳጥን ቁጥር፣ ኢሜይል፤

## ማጣቀሻዎች


1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት አፈጻጸም ማንዋል ሚያዚያ 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ፤
2. ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር እና የህንጻው የውስጥ ዲዛይን ስታንዳርድ ሚያዚያ 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ፤
3. ከተማ ልማት ቤቶች ሚኒስቴር የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ የዜጎች ቻርተር ስታንዳርድ የካቲት 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ፤
4. Ministry of Urban Development and Housing, Urban Planning, Sanitation and Beautification Bureau, Manual for Cemetery Management April, 2015
5. Ministry of Urban Development and Housing, Ethiopian National Urban Green Infrastructure Standard, Addis Ababa, November, 2015
6. Republic of South Africa, Ekurhuleni metropolitan municipality, cemetery and crematorium by laws, 25 April 2007]
7. National Cemetery Administration (NCA), Facilities Design Guide, Department of Veterans Affairs National Cemetery Administration Office of Facilities Management Facilities Quality Office 202-565-6775 June 99